# ብሔረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮጵያ



አዳምኤ
(ግጥሞች)
በዕውቀቱ ሥዩ

Copyright © Bewketu Seyoum 2020

All rights reserved, including the right to reproduce this book thereof in any form whatsoever.

የሽፋን ቅንብር - ሕይወት ማሩ

የደራሲው ሌሎች ሥራዎች

| | | |
|---|---|---|
| የማለዳ ድባብ | (ግጥም) | – 2009 ዓ. ም |
| ከአሜን ባሻገር | (ታሪካዊ ወግ) | – 2008 ዓ. ም |
| መግባትና መውጣት | (ልብወለድ) | – 2002 ዓ. ም |
| ስብስብ ግጥሞች | (ግጥም) | – 2001 ዓ. ም |
| የሣት ዳር ሀሳቦች | (ግጥም) | – 2000 ዓ. ም |
| እንቅልፍ እና እድሜ | (ልብወለድ) | – 1999 ዓ. ም |
| በራሪ ቅጠሎች | (ልብወለድ) | – 1996 ዓ. ም |
| ኗሪ አልባ ጎጆዎች | (ግጥም) | – 1995 ዓ. ም |



## ምስጋና

ያለ መቅዲ (መቅደስ ወርቅነህ)፣ ሕይወት ማሩ እና ብሩክ አብዱ ረድኤት እነዚህ ግጥሞች እንደ ዛር ቆሎ የትም ተበትነው መቅረታቸው ነበር። በፍር ቆጥር የሌለው ምስጋና ይድረሳቸው!

# ማውጫ


በጣጥም መፅናናት 9

ጣንዲት ቃል ይማራል 13
ነጻኔ 14
ለጤዛ ተዋድቀን 15
የምኞት እንቅልብ 16
ካልዳሰሱ አለምንም 17
አልሞትም 18
ባሕር ውስጥ ዝናብ ይለኛል 19
አዳምኤል 20
ማህሌተ ገነበ 21
መኖር ነው የምመኝ 22
ሰብርባሪሽ ወጋኝ 23
ስንቱን እፀድ እስከምነው 24
አይደለም ምኞቴ 25
ያልጣዱት አይበሰልም 26
ሁሉም ለምን ያልፋል? 27
ያመት በዓል ማግስት ትዕይንቶች። 28
መወድስ 30
የመጻተኛው እንኩርኩር 31
ምንሽን 32
ዘመም ይላል እንጂ 34
ኢትዮጵያዊ ነኝ! 36
ተፈጥሮን ደጅ ልጥና 37
ያንቺው ጉረኛ 38
ይድረስ 39
ያው እንደኛው ናቸው 40
ሞቴ በሥርዐት 41

የባከነ ሌሊት 42
አንች ኮርቻ ሰሪ 44
አህያ ሆይ ማረን 45
ንቀን ያለፍነው ቃል 46
መስታወት ፊት ቆሜ እንዲህ እላለሁ 49
እኔ ምፈልገው 50
ሰውረኝ! 52
መወድስ ላርባ ምንጭ ከተማ 54
ውጊያ ሲሆን ኑሮ 55
ቢታነፅ ቢወቀር 56
የመስኮት ዳር ምህላ 57
ለሕዝቡ ብሎ 58
አይመንን አይጨምት 60
በእቅፍሽ ውስጥ ያለው ሰላም 61
ሚሊዮን ፀሐዮች ሚሊዮን ጨለሞች 62
የውበት ጀርባው 63
ሀሳብ ከሐምሌ ጣራ ስር 64
የጥቅምት መስከ ነኝ!! 65
ኖረሽ እይው በቃ 66
በሽንገ ተጀንኘ 68
የተከፈተ በር 69
የሌት ማህሌት 70
ከምነቴ ጋር ቀረሁ 71
ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ 72
ገላ መንገደኛ 74
ላንዲት ድንጋይ ፈላጭ አረጋዊት 75

(የቀላ ግጥሞች) 77

እንደምትወዳት ንገራት! 79

ግጥሎት (ግጥምና ጠሎት) 80
ማዶ ለማዶ 82
ሰው ከቀየው እንጂ 83
ፀደይን በመስኮት 84

አይቆምም ዘፈኑ 86
ለልደቴ፣ 87
የዘንድሮ ነገር 88
አብርሃም፣ በግ፣ ይስሐቅ 89
UUMAMA BIRAAN TA'A! 90
የበሻህውረድ የፍጻሜ ቃል 92

መውጫ 97

## በግጥም መፅናናት

ከተወለድሁ እስከዛሬ ያለውን አራት አስርት አመታት ዞር ብየ ስገመግመው የቀውስ ዘመን ነው። የጦርነት፣ የርሃብ፣ የስደት፣ የስልጣን ብልግና ዜና ያልሰማሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ከመወለዴ በፊት የነበረው ዘመን ምናልባት የከፋ ሳይሆን አይቀርም። ባጫጭር ስንኞች ተቀንብበው በሕዝብ ትውስታ ውስጥ ተመዝግበው የደረሱን ግጥሞች የችግሮችን ተወራራሽነት ያሳያሉ።

ጦርነት :-

ሞጣ ቀራኒዮ፣ ምነው አይታረስ
በሬሳ ላይ መጣሁ፣ ከዚያ እስከዚህ ድረስ።

ስደት :-

መርከብ መጸት ትኬ ተኸዲና
ጐበዝ ኬደ እንጀራ ሀደና
ጓል እኖኻ ትበኪ ደኒና

(ትርጉም ከትግርኛ )

መርከብ መጣች በጭስ ተሸፍና
ወጣትም ነጎደ በእንጀራ ጎዳና
የእናትህም ልጅ ታለቅሳለች ተደፍታ

የስልጣን ብልግና:-

*Hidhii hikii male hundu harka isaati*
*silaa maalsodatta ilma abaa motti*

(ትርጉም ከአፋን ኦሮሞ)

ሁሉ በጅህ ሆኖ፣ ትፈታ ታስራለህ
የንጉሥ ልጅ ሆነህ፣ ማንን ትፈራለህ።

ደግነቱ ይቺ ዓለም ከመከራዋ በየጣልቃው ከበረከቷ ቆንጥራ ታቋድሰናለች። ለኔ ከማፍቀርና መፈቀር የሚገኝ ደስታ፣ ከማወቅ የሚገኝ ፍስሐ እና ከታማኝ ባልንጀራ የሚገኝ ምቾት ሕይወትን ትርጉም የለሽ ከመሆን አድኗታል።

ለብዙዎቻችን ኑሮ ከደስታው ይልቅ መከራውና ፈተናው ያይላል። ኑሯችን በጥቅሉ ሲታይ አንድ ያልታወቀ ባላገር፣

"አላልቅ አለኝ መንገዱ
አንዱን ስወጣው አንዱ"

ብሎ እንዳንጎራጎረው ነው። ዝርዝሩን ስንምሰው ግን አንዳንድ ጸጋ አናጣበትም። በመንገዳችን ላይ የእረፍት ጣቢያ፣ የድግስ ቦታ፣ የሚያምር አፀድ፣ የሚያስመካ ወዳጅ፣ የሚያኮራ ገድል ሊያጋጥመን ይችላል።

ዘመናት እንደ ግለሰቦች የእድል ሰለባዎች ናቸው። አንዳንዱ ዘመን ደሞ ከሌላው ዘመን የበለጠ ፈተና ይበዛበታል። እነሆን ግጥሞች ከየቦታው ለቅሜ ለመጽሐፍ በማሰናዳበት ጊዜ ዓለም በወረርሽኝ እየተናወጠች ነው። እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥም ብዙ ሰዎች በእምነታቸው መፅናናትን ያገኛሉ። የተወሰኑት ሰዎች ደግሞ ከፍልስፍና ውስጥ ፍቺ ለማግኘት ይሞክራሉ። ኪነጥበብን ብቸኛው አፅናኝ አድርገን የምንወስድ ሰዎችም አለን። በዚህ ሁሉ ከተፈጥሮ እና ከማህበረሰብ በሚመነጭ ድቀት መሀል ጨዋታ ባይኖር፣ ተረት ባይኖር፣ ግጥም ተውኔትና ጣዕመ ዜማ ባይኖር ምን ይውጠን ነበር?

ኪነጥበብ የሥቃይ ማርከሻ መሆኗን የሚያስረዳ አንድ ትውፊታዊ ትረካ ትዝ ይለኛል። አፄ ገብረመስቀል ዘመን ነው አሉ፣ ማህሌታይ ያሬድ በአክሱም ቤተመንግሥት ተጋብዞ በንጉሡ ፊት ዝማሬ ያቀርባል። ንጉሡ በዝማሬው ጣዕም ከመመሰጡ ብዛት የተነሳ በእጁ በያዘው ጦር ወይም ዘንግ የያሬድን እግር ይወጋዋል፣ ከያሬድ እግር የፈሰሰው ደም



የቤተመንግሥቱን ወለል አጥለቀለቀው። ንጉሡ መውጋቱን ያሬድ መወጋቱን ያወቁት ዝማሬው ካለቀ በኋላ ነው።

ይህንን ትረካ የጻፉት ሰውየ ወይም ሴትዮ በዚህ ዓለም ያለው ሥቃይ ባብዛኛው ሰው ሰራሽ ነው። ሥቃዩን የሚያቃልለውም የኪነት ሥራ ነው የሚል ቁምነገር ሊነግሩን የፈለጉ አይመስልም? ለጊዜው ሥቃዩን ከሥሩ ፈንቅለን ማስወገድ ባንችል እንኳን በማቅለያው እየተፅናናን እንቆይ።

## ባንዲት ቃል ይጫራል

ጉልቤው ቢደባባይ፣ ድሃውን ሲበድል
ድምፅህን አጠብድል
ቃል፣ ሩምታ፣ ተኩስ
አውቆ የተዘጋ፣ ጆሮ የሚነድል
ባንዲት ቃል ይጫራል፣ ያንድ ዘመን ገድል።

## ኑዛዜ

ማን ነበር እንደኔ
ከየፅዋው ቀማሽ
ከጭን ሸለቆ ስር፣ የገነት ምንጭ ማሽ
አሁን እዚህ ሆኘ
ከኪሴ እያወጣሁ፣ ዘመኔን ስደምር
ከመኖር አርፌ፣ ማስታወስ ስጀምር

ከጣፋጩ ብትይ፣ ወይም ከሚመረው
ያንቺ ጣም ብቻ ነው፣ አፌ ላይ የቀረው።



## ለጤዛ ተዋድቀን

"ኢድሜያችን ሰባ ነው፣ ቢበዛም ሰማንያ"
ይህም ኑሮ ሆኖ፣ ጠዋት ማታ ፍልሚያ

አንዱ ካንዱ ጥዋ፣ ጥቃት የቀመሰ
በየደጃፉ ላይ፣ ምሽግ እየማሰ
ጦር እንደ ቄጤማ፣ እየነሰነሰ
መንደሩን ሸንሽኖ፣ ባጋም እሾህ ቅጥር
ወገን እያስለየ፣ ባስለፈን ቁጥር

ጤናችን ሲሸረፍ
ቀናችን ሲዘረፍ
የት ሸሽተን እንትረፍ
የት ገብተን እንረፍ?

በዶፍ ዝናብ አገር፣ ለጤዛ ተዋድቀን
ሰላም እንደራበን፣ ደስታ እንደናፈቀን
ትግላችን ስልፉችን፣ ያከትማል አንድቀን።

## የምኞት እንቀልባ

ንጹህ ውሃ ቋጥሮ
የሚዞር ደመና
አየር ላይ ተጋግሮ
አልወርድ ያለ መና
ከስር አለሁ እኔ
በጥምና ጠኔ
በችፍርግ ቁመና።

ምኞት በስስ ጀርባ
ከሸረሪት ፈትል
በተሰራ እንቀልባ
ና ልዘልህ አለኝ
ምኘው ብሳፈር፣ እምዘግዝጎ ጣለኝ።



## ካልዳሰስኩ አላምንም

ሊነጋ ነው ሲሉኝ፣ ለኮስኩት ፋኖሴን
ሊውብቅ ነው ሲሉኝ፣ ደረብኩት በርኖሴን
ሰላም ወርዷል ሲሉኝ፣ ጋሻዬን አራገፍኩ
ሰው አልሰማ ብል ነው፣ ከፉ ቀኔን ያለፍኩ።

ቃል ገብቶ ቃል ማፍረስ
ያገር ልማድ ሁኗል
እንጀራ እንደ መብላት፣ በበሬ እንደማረስ።

ፍቅር ሥጋ ለብሶ፣ በጁ ካላቀፈኝ
ተስፋም ብብቴ ስር፣ ገብቶ ካልደገፈኝ
ኢምንት ነው ምንም
ካልዳሰስኩ አላምንም።

## አልሞትም

ስሚ!
እኔ በዚህ ዓለም፣ ብዙ ብሰቃይም
አንድ ሀሙስ የቀረው፣ መስየ ብታይም
አምሮቴን ሳላገኝ፣ ሱሴን ሳላከትም
በመሬት ከርስ ውስጥ፣ ገላየን አልከትም

አልሞትም!

ማንም ባልደፈረው፣ መንገድ ሳልገሰግስ
እንደ ንጉሥ አይዙር*፣ ግማሽ ቀን ሳልነግስ
በጠገበው ሳልስቅ፣ ለራበው ሳልደግስ

አልሞትም!

ዝማሜን ሳላውቅ፣ ያንደበቴን ግድብ
ዙፋን ላይ ሳልሸና፣ ጌቶችን ሳልሰድብ
ከድሃ ሳላብር፣ ካገሬው ሳልወግን
ከምድር በረከት፣ ድርሻየን ሳልዘግን

አልሞትም!

ስሚ!
ልቤ እንደምኞቱ፣ ቢያገኝ እንደምርጫው
ያላማየ ማብቂያ፣ አንቺ ነሽ መቋጫው
እና
አገሬን ለቅቄ፣ ልብሽ ላይ ሳልከትም
በውብ ከንፈርሽ ላይ፣ ከንፈሬን ሳላትም

አልሞትም!

---

*አይዙር፣ (በእ ...



## ባሕር ውስጥ ገብቶ ይተኛል

ምናልባት አማልከት ካሉ
ካላቸው ህልውና
ሰዎች ሆይ ሰብሰብ በሉ
እንሰዋላቸው ምስጋና!!

አጣድፈው ስለሚጠሩን
ለዘላለም እንድንኖር፣ አድርገው ስላልፈጠሩን!
መጭውን ከፋት እንዳናይ፣ ባጭር ስለሚያስቀሩን
እድሉን እንኳን ቢያገኝ፣ ሁሌ መኖር ማን ይመኛል?
ዓባይ እንኳን ባዝኖ ባዝኖ፣ ባሕር ውስጥ ገብቶ ይተኛል።

(መነሻ ሀሳብ A. Charles Swinburne)

## አዳምኤል

ካፈርና እስትንፋስ እንደተፈጠረ
ሰው መላክ ነበረ!
ከእግዜር ተጣላና፣ ምድር ላይ ወደቀ
ከንፉን ተነጠቀ።

ግን እግዜር ደግ ነው፣ አልጨከነም በሰው
ከንፎቹን ቢቀማው፣ እንቅልፍ ሰጥቶ ካሰው።

ታድያ ከዚያ ወዲህ
ሰውም ሳያስበው
መላእክትነቱ ከልጓም ሲሰበው
ላባ ባያበቅል
በላባ ፍራሽ ላይ፣ ሲገላበጥ ያድራል
ህልሙን ተፈናጦ፣ እንዳሻው ይበርራል።



## ማህሌተ ገንቦ

ባጭር ቀረን ስንል፣ እድሜ ላበደሩን
ቀርፀው ላሳመሩን
ለኩሰው ላበሩን

ቺርስ!!

ፊታችንን አይተው እንደተቸገርነ፣ ካይናችን ላወቁ
ስለማርያም ብለን እስከንለምናቸው፣ ቆመው ላልጠበቁ

ቺርስ!!

ወድቀው ለማይጥሉ፣ ነግሠው ለሚያነግሡ
ነውራችንን አይተው፣ ልክ እንደ ድመት ኩስ ለሚያለባብሱ
ብድር አበድረው፣ ፈጥነው ለሚረሱ

ቺርስ!

ላባ ላረጉልን፣ የመከራ ሸክሙን
ቀልደው ላሳቁን፣ ተጫውተው ላከሙን
በቸከ ዘመን ላይ
ሥጋ ለበስ ትንግርት፣ ሆነው ላስደመሙን

ቺርስ!!!!

## መኖር ነው የምመኝ

በማይ በምሰማው
አንዳንዴ ስገረም
ሕይወት ከናላማው
ስሕተት ይሆን እንዴ? በሞት የሚታረም
ማለት ይቃጣኛል
የዚህ ዓለም ኑሮ
ጥያቄ ወርውሮ
ምላሽ ያሳጣኛል።

ደሞ አንዳንዴ ሳሰብ
ስለሰው ልጅ ሥራ
የሰናፍጭ ቅንጣት፣ በምታከል ጥበብ
የሚገድ ተራራ
በጨለመ ምድር፣ ብርሃን ሚዘራ
በሰማይ ጎዳና፣ ወፍ የሚያሰማራ
ባሕርን የሚያጠምድ፣ መብረቅ የሚገራ
ከቀለሞች መሃል፣ ምስል የሚያነቃ
ከዝምታ መሃል፣ የሚያፈልቅ ሙዚቃ

በቃሉ በጣቱ
በቅመም ቅንጣቱ
ዘልቆ የሚያከመኝ
እንደሳንዱቅ ከፍቶ፣ መልሶ ሚገጥመኝ
ይህንን ሁሉ ሳይ ሕይወት እየጣመኝ

መኖር! መኖር! መኖር! መኖር ነው የምመኝ።



## ስብርባሪሽ ወጋኝ

ሁሌ እምነመጅሽ
ሁልዜ እማልምሽ
የንጉሥ ብርሌ
የግርማዊ ከንፈር
ወትሮ የሚቀስምሽ
የምታረኪለት፣ የድለኛውን ጥም
እኔ ግን ምስኪኑ
ሲሳይሽ ባይደርሰኝ፣ ከአዳሽ አላመልጥም
ያንፀባረቅሽ ዕለት፣ ግርማሽ ያላስጠጋኝ
ዛሬ ብትወድቂ፣ ስብርባሪሽ ወጋኝ!!

## ስንቱን አፀድ አከሰምነው

ያገራችን ቦለቲካ በሁለት ቃል ሲደመደም
ምኒልክ ይቅደም!
ምኒልክ ይውደም!
----

መቸም ያዳም ልጅ መሆን፣ የማይፈታ ጣጣ
ሁለመናው ሲዞርብን፣ የመኖር ሰበብ ስናጣ
ጉልበትና ሥልጣን ኖሮን፣ ንብረት መሬት ባንደለድል
እንዳባቶች፣ እንደናቶች፣ ዘምተን ታጥቀን ባንገድል
ለሱስ ያህል ያምረናል ጦር፣ ላመል ያህል ያምረናል ድል።

አልፎ ሂያጆች ሆነን ሳለ፣ ደማቅ ድንበር አስምረን
በመናኛ ድንኳን ዙርያ፣ የኮረንቲ ቅፅር አጥረን
ያብሮ መኖር መላ ጠፍቶን፣ ያብሮ መሞት ዘዴ ፈጥረን
ከቤታችን ጠብ ቢጠፋ፣ ከጎረቤት ተበድረን

በየሱስ ስም በማርያም ስም
በነ ሌኒን በማርክስም
ዛሬ ደሞ በምኒልክ
ባገኘነው ወዳጅ መጠን፣ ባፈራነው የጠላት ልክ
ዋጋችንን ስንተምነው
ስንቱን ቀትር፣ አጨለምነው
ስንቱን አፀድ፣ አከሰምነው?!

## አይደለም ምኞቴ

አይደለም ምኞቴ
ለምለም አንገትሽ ላይ፣ ከንፆቼን መጠምጠም
ዳሌሽ ላይ መንሳፈፍ፣ ጭንሽ መሃል መስጠም

አይደለም ምኞቴ

ከንፈርሽን ማለብ
ቀሚስሽን መግለብ
ከገላሽ ቆርሼ፣ ገላየን መቀለብ
ደረትሽን ማለም
ጡትሽን መሳለም
በቁንጅናሽ ጅረት፣ ገነቴን ማለምለም
ዓላማየ አይደለም።

ምኞቴን ልንገርሽ?

ካለሺበት ቦታ፣ ቀልቤን ማስማራት
ወትሮ ካንቺ ጋራ፣ ቡና መጠራራት
ሰላም መገባበዝ፣ ትዝታ መጋራት

የጨለመ ፊቴን፣ ባይንሽ ጮራ ማድመቅ
በቃላትሽ መስከን፣ በሣቅሽ መጠመቅ
በጎ መንፈስሽን፣ ካይንሽ ላይ መሻማት
ርጋታሽን ማጥመድ፣ ዝምታሽን መስማት።

## ያልጣዱት አይበስልም

ፍቅር እንደ ዝናብ፣ ከሰማይ አይወርድም
ያበባ መደብ ነው
በሰው የሚታነፅ፣ በሰው የሚወድም
ተዘርቶብን እንጂ፣ ተሰብከን አንወድም።

"ወዳጅ ወዳጅ"፣ የሚያቀነቅኑ
አገር ያቀኑ ለት፣ መች ልብን አቀኑ

ሳይወጡ ሳይወርዱ
ውብ ሥራን ከውብ ቃል፣ ሳያስተባብሩ
ከድሜ እና ከምኞት፣ ቆርሰው ሳይገብሩ
ፍቅር መች ይፈልቃል?
በስብከት በምልጃ፣ በየዋህ ሰዎች ህልም
ያልጣዱት አይበስልም
ያልዘሩት አይበቅልም።



## ሁሉም ለምን ያልፋል?

የጣፈንታ መዳፍ
ደስታና መከራን፣ እያፈሰ ሲናኝ
"ሁሉም ያልፋል" ብሎ፣ ማነው የሚያፅናናኝ?

ግራ በተጋባ፣ በዞረበት አገር
ካንቺ የምጋራው፣ ሠናይ ሠናይ ነገር
ፊቴን የሚያበራው፣ ያይንሽ ላይ ወጋገን
ዛሬ ተለኩሶ፣ የሚያሳየኝ ነገን
ለምን ሲባል ይለፍ፣ ያንን መሳይ ፍቅር
ደስታሽ ይገተር፣ ሣቅሽ ቆሞ ይቅር!!

በብሩህ ቀለማት የተሸላለመ
የተዋበ ህልሜ
በሁለት ጦርነት፣ መካከል የቆመ
አጭሩ ሰላሜ
ያፍላነት ወኔየ፣ የጉርምስና አቅሜ
ነበር ተብሎ እንዳይቀር፣ እንዳገኘው ወትሮ
ባለበት ላይ ይቁም፣ ባስማት ተገትሮ

እና

ከጣፈንታ መዳፍ፣ ሞልቶ ከሚፈሰው
በሰው የሚደርሰው
ለሰው የሚደርሰው
በጊዜ ኬላ ላይ ተዘዋውሮ ሲሰለፍ

## የሙት በዓል ማግስት ትዕይንቶች!!

የሞላ ሸንትቤት
ጭር ያለ ቤተሰብ
የተጠረገ ድስት፣ ድርቅ የመታው ምሰብ!!

ያደፈ ቁጤማ
በበግ በሰው እግር፣ የተደቀደቀ
ወዙ ባንድ ሌሊት፣ ተመጦ ያለቀ
መጥረጊያ ሚጠብቅ፣ ወድቆ ተበታትኖ
ትናንት ጌጥ የነበር፣ ዛሬ ጉድፍ ሆኖ!!

የተወቀጠ ፊት፣ የነጋበት ድንገት
በዳንኪራ ብዛት፣ ወለም ያለው አንገት
የዞረበት ናላ፣ ጌሾ ያበከተው
እንኳንስ መገንዘብ፣ መጀዘብ ያቃተው
የወለቀ ወገብ፣ የዛለ ትከሻ
መኪና ይመስል፣ ብየዳ የሚሻ።

የጠጅና የጢስ፣ ድብልቅ አስትንፋስ
ከሆድ ሸለቆ ውስጥ፣ የታፈነ ነፋስ
ባንጀት የታሰረው
እንደተከበበ አመፀኛ ሽፍታ
መውጫ የቸገረው!

የማይፈካ ሰማይ፣ የማይዘንብ ደመና
በላባና በፈርስ፣ ያደፈ ጎዳና
በበግ ራስ ምላስ፣ የተልከሰከሰ
የጠገበ ውሻ
በመንፈቅ አንድ ጊዜ፣ አጥንት የቀመሰ።

ሆነበር ያዛገው፣ መሂና አሽከርካሪ
እግረኛ አስደንባሪ
በከፊል የነቃ፣ በከፊል የተኛ



ከሱ የማይሻል፣ የመኪና እረኛ
ካውራ ጎዳናው ዳር፣ ቁሞ ሚያንቀላፋ
ድብርትን ባናቱ፣ እንደ ቆብ የደፋ!!

የተድላ ማገዶ!!
ላጭር ጊዜ ነዶ
ላጭር ጊዜ ደምቆ
ላጭር ጊዜ ሙቆ
አመዱ ብዙ ነው፣ እያልቅም ተገዝቆ!!

## መወድስ

ፊትሽ እንደ ምሥራቅ፣ ብርሃን ያመርታል
ፈገግታሽ ዋስ ሆኖ፣ እስረኛ ያስፈታል
ውይ መዓዛሽ ሲያምር!
የሎሚ የንጆሪ፣ የኮከ ሽታ ድምር።

ከየዛፉ ቅጠል
ንፋስ በከንዶቹ፣ ከሚሰበስበው
ከሳሩ ከሰርዶው፣ መሬት ከሚሳበው
በደብር አፀድ ላይ፣ ከሰፈነው ለምለም
ከየኔኪታሩ ጣም፣ ከያበባው ቀለም
አውጣጥቶ ማን ሰጠሽ?
እንዲህ ምን አስጌጠሽ
እንዲህ ምን አሰላሽ?
መች ተጣድሽ? መች ፈላሽ?
ለዛሽ በፊትሽ ላይ መች ተጠነሰሰ
ውበትሽ ምንገድ ላይ፣ ገንፍሎ ፈሰሰ

ገላየ ጭንቅ አይችል፣ ዐይንሽ ሰውር መቀስ
ኧረ ቀስ! ኧረ ቀስ!
ከደም ከሥጋ እንጂ፣ አልተሰራም ካለት
በውበትሽ አምላክ፣ ለልቤ አዘኝለት!




## የመጻተኛው እንጉርጉሮ

ያኔ ዋዛ ሳለ፣ ግድግዳ ጣራ በር
"ዞሮ ዞሮ ከቤት" ይሉት ብሂል ነበር።
ለንስር ጎጆ አለው፣ ለከብት አለው በረት
የኔናንቺ ድርሻ
ቤት ጎምዥቶ መቅረት
አገር ናፍቆ መቅረት
መንገድ አቅፎ መቅረት
ዞሮ ዞሮ ዞሮ እንደገና ዙረት።

## ምንሽን

የሰው አገር ሙጥኝ ብየ፣ በወጣሁበት እንዳልቀር
አገሬ ፍቅርሽ ሳበኝ፣ ግና ምንድር ነው ማፍቀር?
እንዳስመሳይ አዝማሪ፣ ካልሸነገልኩሽ በቀር
ከተወለድሁ እስተዛሬ፣ ከጣትሽ መች ጎርሼ
ወተትሽን መች ቀምሼ
ወለላሽን መች ልሼ?

ሲርበኝ
ጠኔ በቀኝ በግራ፣ እንደ ጭፍራ ሲከበኝ
የት ነበር የንጀራሽ ሌማት?
ሾላ ስለቅም ተሻምቼ፣ ከሽመላ ከማማት
ኑሮየ ሁዳዴ ጦም፣ ፋሲካ አልባ ሕማማት
እና ከድሎት አገር፣ የሲሳይ ዶፍ ከሚያወርደው
ምን ገፍቶኝ ነው በሞቴ? ወዳንቺ ምሰደደው
ምን ነክቶኝ ነው? ምንሽን ነው የምወደው?

እኔና ብጤዎቼ፣ እኛ ቅብዝብዝ ልጆችሽ
መስኮት በሩ ተዘግቶብን፣ ተበትነን በደጆችሽ
ይሄው ሶስት ሺ ዘበን፣ ወደ ሰማይ አንጋጠን
በንዝርት እግር ተንበርክከን፣ በቀይ ዕንባ ስንማጠን
የለት እንጀራችንን ነፍጎ፣ የለት ገጀራችንን ሰጠን።

አሁንም ለመከራሽ፣ ማን አለና የሚገደው
እሪታሽ እንደዘፈን፣ ያለም ጆሮ ለመደው
እና ምንሽ ነው ሚስበኝ? ምንሽን ነው የምወደው?

ዛሬም ሆነ ያለፈው
በላባ ብእርም ይሁን፣ በኪቦርድሽ የተጻፈው
ታሪከሽን ሳነበው፣ ደምና አመድ ነው የሞላው
መች ተነቅሎ ከወለልሽ፣ የሾህ ጉንጉን አሜኬላው
መች ተጥሶ ያውቃልና፣ የጭቆናሽ ዘመን ኬላው
ሥልጣን ፈልሶ ቢሸጋገር፣ ካንዱ ጭራቅ ወደሌላው።

እናም እንሆ!
ያለፈውን ዘመን ትቼ፣ የቀረኝን እያሰላሁ
የብርሃን ቅሪት ባጣ፣ አምፖሌን በተስፋ ሞላሁ
እንጀራየን እን[illegible] ሀሰን* በዳበሳ እየበላሁ።

ከዚህ ወድያ አልልሽም፣ ወዴት አለ ያንቺ አለኝታ
ግን ምንሽ ነው የሚስበኝ? ልማድ ይሆን ወይ ይሉኝታ?
አግሬን ከምድርሽ ጋራ፣ ምንድነው ያስተሳሰረው
ያገር ፍቅር አለኝ ብልስ፣ ምንሽን ነው የማፈቅረው?

---

*ሀሰን ተብሎ የተጠቀሰው (ሀሰን አማኑ የተባለው ዝነኛው ዐይነስውር
የወሎ አዝማሪ ነው።)

እንደ ጊዜው መከፋት
እንደ ግፉ መስፋት
እንዳገሩ ከስመት
እንዳገሬው ጥመት

እንደሰዉ ጭካኔ፣ እንደ ልቡ ፍሬ
ታምር ነው መትረፍሽ፣ ታምር ነው መኖሬ።

የበጎ ሰው ሀሳብ፣ ሲካድ ዕለት በለት
ጉድጓድ ተምሰለት
ስብእና ሲቀበር፣
በዚህ ምድር መኖር፣ አያስመኝም ነበር።
ምድሩ ሳር ቅጠሉ፣ በስጋት ተሞልቶ
የማለዳው ሰማይ፣ እንዳንቀልባ ቀልቶ

ታረደ
ነደደ

ከዘብጥያ ወጥቶ
ዘብጥያ ወረደ
የሚል ዜና ብቻ አየሩን ሲሞላው
ሰው በገዛ ጥላው
በርግጎ ሲሸበር
በዚህ ምድር መኖር፣ አያስመኝም ነበር።

አዎ

ለጊዜውም ቢሆን፣ ግፍ ያደነዝዛል
በደል ያስተከዛል
ጊዜም ጠብን ሸሮ፣ ወደ ፊት ይጓዛል
በልብ ሰሌዳ ላይ፣ ቂም ይደበዝዛል
በነገ ያመነ



ልጁን ቀብሮ መጥቶ፣ ሚስቱን ያስረግዛል።

ይቅርታና ምሕረት
ፍቅርና ህብረት
ከግፍ ጋር ፍልሚያቸው፣ ቢሆን የሞት ሽረት
ዳገት ይወጣሉ፣ በንጥፍጣፊ አቅም
የመኖር ፍላጎት
ዘመም ይላል እንጂ፣ ተገርስሶ አይወድቅም።

## ኢትዮጵያዊ ነን!

ፈቅደን ሲመሩን፣ ቾቦ ተቀባይ
ለሚነዱን ግን፣ አሻፈረን ባይ
ካልነኩን በቀር፣ ቀድመን ማንዘምት
ከጋሻ በፊት፣ ጦር የማንሸምት

ኢትዮጵያዊ ነን!

ህብር ያስጌጠው፣ ሕይወት ለማብቀል
ዘር ሳናጣራ፣ የምንዳቀል
ለነዱን ሰይጣን፣ ለመሩን ሠናይ
ጌታን ከገባር፣ ለይተን ምናይ

ኢትዮጵያዊ ነን!

ብዙ ህልሞችን፣ ወዳንድ ዓላማ
የሰበሰበ፣ ገርቶ ያስማማ
በደምና ላብ፣ ያቆምነው ካስማ
አገዳ አይደለም፣ የሚቀነጠስ
የዝምድናችን መተሳሰርያ
ሺ ጊዜ ቢከር፣ የማይበጠስ

ኢትዮጵያዊ ነን!

ምን ሆድ ቢብሰን፣ ምን ብንቸገር
አድር አይፈርስም፣ እንኳንስ አገር
ብለን በትግስት፣ የምንሻገር
ሲገፈትረን፣ ግፈኛና አጥቂ
ቁልቁል ሲሰደን፣ ሸቅብ መጣቂ
ለውርደት ሲያጩን፣ የምንጀነን

ኢትዮጵያዊ ነን!




## ተፈጥሮን ደጅ ልጥና

"እኔ ልሙትልሽ" እያልኩኝ አልምልም
ቃላቴን መንዝሬ፣ ለሞት ቀብድ አልከፍልም

ያኔ ትዝ ይልሻል?
"ራስህን ግደል" ብለሽ፣ በረኪና የላከሽልኝ ጊዜ
አድሜ ለስጦታሽ፣ ታጠበ ሸሚዜ።

ገደብ ጫፍ በሌለው፣ በልቤ መጋዘን
ቢታጨቅ መከራ፣ ቢጠራቀም ሀዘን
"ባለፈልኝ" እንጂ "በሞትኩ" ብየ አላቅም
ካልጋ ላይ ነው እንጂ፣ ከፎቅ ላይ አልወድቅም።

በሀኪሙ ስተት፣ በቁሜ ብከፈን
በወርድ በቁመቴ፣ ሳጥኔ ቢደፈን
ከጭስ አቀጥናለሁ፣ እኔ መውጫ አላጣም
በጠጅ በወይን አገር፣ ሸጉጤን አልጠጣም።

የተመደበልኝ ዘመን ከባከነ
የተሰፈረልኝ ቀን አልቆ ከሆነ
ተፈጥሮን ደጅ ልጥና
ባዲስ መንገድ ትስራኝ፣ ባዲስ የፍጥረት ውል
መስኮትሽ ላይ ሆና
ስትዘምር የምትውል
ድንቢጥ ወፍ ታድርገኝ
ብኖር አንቺን እየሁ፣ ከመሞት ምን ሊገኝ።

## ያንቺው ጉረኛ

አነጋገሬ የሰለጠነ
አረማመዴ የተመጠነ

ስደሰት ፊቴ፣ የግዚሀር ባውዛ
ስስም ከንፈሬ፣ ያበባ ጤዛ
ካለት ያወጋሁ፣ ከንብ የተጋሁ

እንደ ዘንገና፣ ውሃ የረጋሁ
ከጎህ ቀድሜ፣ ባይንሽ የነጋሁ።

ባሳብ በመላ፣ ብናገር እውነት
ባቅፍሽ ከንዶቼ፣ የሐር መቀነት።

ጣትሽ ደባብሶኝ፣ ጥፍርሽ ቢበጣኝ
ዘቢብ ነው እንጂ፣ መች ደም ሊወጣኝ።

ለምድር ቢቀርብ፣ ቁመቴ ቢያጥር
በጎልያድ ግንባር፣ የማነጣጥር
ልቤ በጣቱ፣ ሰማይ ሚነካ
ከነራስ ደጀን፣ ከንጠጠ የካ
ቁመት በኩራት፣ የሚለካካ

ብትደገፊኝ፣ የላባ ፍራሽ
ብትመገቢኝ፣ የመና ቁራሽ።

እንኳን በጃኖ፣ እንኳን በሱፉ
እንደ ቁጥቋጠው፣ ልክ እንደዛፉ
ቅጠል ለብሼ፣ የምሽቀረቀር
የተለጋ ልብ፣ ቀልቤ ማስቀር

ያንቺው በረኛ
ያንቺው ቁንን ነኝ፣ ያንቺው ጉረኛ።



## ይድረስ

እኔ የማውቀው፣ መለዮ ለባሽ
የገባሮች እንባ አባሽ
የግፍ ማዕበል ቀልባሽ
የደከመ ሚያበረታ፣ የዘመመ የሚደግፍ
የኑሮን ሸክም እንደ ሾላ፣ ከጫንቃ ላይ የሚያራግፍ።

አንተ ግን
የጀግኖችን ልብስ ለብሰህ
ከኑሯችን ጭነት ብሰህ .
ላገርህ እንኳን ባትሞት፣ አገርህን ትገላለህ?
እንዴት እንደ ወረርሺኝ፣ በመደዳ ትጥላለህ
በላቡ ያወዛህ ገባር፣ የቀለበህ ጥሮ ግሮ
ተርቦ ያጎረሰህ፣ በሊጋስ ምጣዱ ጋግሮ
አቤት ብሎ ቢጮህልህ፣ መሄጃ አጥቶ ተቸግሮ
ልጁን ቤቱን ስታሸብር
ደረቱን በጥይት ስትገምስ፣ ጐኑን ቅልጥሙን ስትሰብር
ትንሽ እንኳን አታፍርም?
ህሊና ባይኖርህስ፣ ከሰው አትበደርም?

ያልገነባኸውን ስታፈርስ፣ ያልፈጠርከውን ስትገድል
ለራበው ለተቸገረ፣ ሞትን እንደ ቆሎ ስታድል
ስታወድም ስታከስም፣ ስትፈነክት ስታቆስል
ሁሌም ቃታ ስትስብ፣ ሁሌም ሳንጃህን ስትስል
የሰለባህን ቀሪ እድሜ፣ መውሰድ የምትችል ይመስል
የምትበላው ይስማማሃል፣ ከምትጠጣው ትስማማለህ?
ደም በላሱ ከንፈሮችህ፣ ልጆችህን ትስማለህ?

## ያው እንደኛው ናቸው

በሰማይ አዋፋት፣ አይዘሩም አያጭዱም
አገር አቆራርጠው፣ ሲራራ አይነግዱም
ግን ከኛ ኑሮ ምን ልዩ አረጋቸው?
ለእፍኝ እድሜ ሲባል፣ የሳር ጎጆ ማልማት
ሞላሁ ለማይል ሆድ፣ እህል በመሻማት
ያው እንደኛው ናቸው።

ያለም ከበርቴዎች
በፈጣን ጀታቸው፤ ሰማዩን ቢገምሱም
ርካታ ካለበት፣ ቀድመውን አይደርሱም
ሻርክ ተፈናጠው፣ ከባህር ቢጠልቁም
መንኰራኵር ጋልበው፣ ከጠፈር ቢመጥቁም
እኛን ከሚያሰጋን፣ አንድ ርምጃ አይርቁም።

የምድሪቱ ጌቶች
ለሰው ዐይን ሞልተው
ትልልቅ ቢመስሉም፣
በኵራት ተነፍተው
ተራራ ቢያከሉም፣
ከተሽከሸኩ፣ አንድ እፍኝ አይሞሉም።

ፍትወትና ፍራት፣ የሚጎትታቸው
ያው እንደኛው ናቸው፣
ባለስትንፋስ ሁላ፣ ቢታይ ተመንዝሮ
በቁመት አይበልጥም፣ ጎልያድ ከሰንዝሮ
ለየቅል መሳዩ፣ ያው ነው ዞሮ ዞሮ።



## ሞቱ በሥርዐት

ጥሩንባ ተነፋ
ህልፈት ተለፈፈ
እድር ቢያሰማራው፣ ሕዝቤ ተሰለፈ
የቅፀር ጥድ መስሎ፣ የተከረከመ
በስልት እየሄደ፣ በወግ እየቆመ
ፖሊስ ከነ ማርሹ
ቄሱ ከነፅናው
ከሳሹ ወራሹ
ወዲህ አስለቃሹ፣ ወዲህ የሚያፅናናው
ሁሉም ባጀብ ያልፋል፣ በፈሊጥ በፈናው።

ከቀብር መልስ ግን፣ የንቧይ ቤት ሆነና
ተቀልሷል ሲባል፣ ተመልሶ መና
መንገድ ላይ ሲጋፋ
ሲራኮት ሲዳፋ
ለቀለብ ሲዋደቅ
ይቺን በመገፍተር፣ ያንን በመደቅደቅ
ጭምቱን ሲያቀውስ፣ የበሰለን ሲያምስ
ደንብ እያበላሸ፣ ቅፀር ሲደረምስ
ሞቱ በሥርዐት፣ ኑሮው በትርምስ።

## የባከነ ሌሊት

ወይ ሮንድ አላደርኩ
ወይ ኰከብ አልቆጠርኩ
ወይ ደልቶኝ አልጨፈርሁ
ወይ ውስኪ አልተዳፈርሁ
ወይ ስአታት ቆሜ
ቤተስኪያን ስሜ
ሰይጣን አላሳፈርሁ።

ሌቦች ደብድበውት
አንዱን ምስኪን ላሥር
ባምቢስ ድልድዩ ስር
ቆስሎ የወደቀ
ገላው በላዩ ላይ፣ እንደጨርቅ ያለቀ
ፊቱ ተሸፍኖ በደምና አቧራ
"በዑራኤል ርዱኝ" ብሎ የሚጣራ
ምስኪን አባወራ
ብብት ስር ገብቼ
አፋፍሼ አንስቼ
ተሸከሜ አድኜ
ስፈልግ አምቡላንስ፣ ሲሻኝ ዶክተር ሆኜ
ወይ ምግባር አልሰራሁ
ወይ ጀብድ አልፈጸምኩኝ፣ ወይ ጽድቅ አላፈራሁ።

አንድ በትረ ሙሴ
ሁለት ስስ አሎሎ
ከጭኔ መሀከል ሲያመሽ ተንጠልጥሎ
ሲባክን ዝም ብሎ
"እሸኝ የኔ ጀግና እንደሰነፍ ቆሎ"
የምትል መለሎ
ልቤን ሳትሰውረው
አልጋዬን ሳትሰብረው።

ወግ ቢጤ ሞንጭሬ፣ ፌስቡክ ላይ ሳልለጥፍ
"እናትዋን ጨረቃ" የሚል ግጥም ሳልጽፍ።

አንዲት ሴት አዳሪ፣ ቺቺንያ ምንገድ ላይ
ዕድሏ.ሰባራ ሰውነቷ አማላይ
ካፍያውና እንባዋ ተጋግዞ ሚያረጥባት
ደምበኛ ስትጠብቅ ደመኛ ጥሎባት
አምስት ደፋሪዎች ከበው ሲያዋክቧት
ሲገፉ ሲስቧት
"ኧረ በናታችሁ በወላድ ማሕፀን
እህት የላችሁም?" ብላ ስትማፀን
ልመናዋ ሰቦኝ
እንዳበጀ በለው፣ በደሏ አንገብግቦኝ
ከኋላ ደርሼ
ነበልባል ለብሼ፣ ነበልባል ጎርሼ
እንደብሩስሊ፣ እንዳየሩ ጋኔን
እግሬን ወንጨፍ ወንጨፍ
ወዝወዝ ወዝወዝ ጎኔን
በማረግ ቃኝቼ
ከኋላ ነው ሲሉኝ ከፊት ተገኝቼ
ካምስቱ መካከል አራቱን ነጥየ
ከቻልኩ በካራቴ ካልቻልኩ በሣቅ ጥየ።
ድል ሳላስመዘግብ
ውጥረት ሳላረግብ
ወይ ታሪክ ሳልሰራ ወይ ታሪክ ሳልዘግብ
ያለ ምንም ጣጣ ያለምንም ጸጋ
አለሰበብ መሽቶ አለሰበብ ነጋ።

## አንችኮ ርቻ ሰሪ

አንች ኮርቻ ሰሪ
ሳንቃውን አቅልይ፣ ጠርዙን አለስልሺ
ያንዱ ፍጡር ወንበር
ላንዱ ፍጡር ቀንበር
መሆኑን አትርሺ።



## አህያ ሆይ ማረን

የዘራም አጨደ
ያጨደም አስገባ
ያስገባም ጋገረ
የጋገረም በላ
ከዚያ ምን ይመጣል
ፍርፍር ሆኖ ገብቶ፣ ፍግ ሁኖ ይወጣል።

በሽመታም ይሁን፣ በወራሪ ዝርፍያ
በሥርዐት ይሁን፣ በሽምያ በግፍያ
በግብግባም ይድረሰን፣ ወይ በመቀላወጥ
የምንበላው ኅብስት፣ የምንጨልፈው ወጥ
ማለፍያው ሰርገኛው፣ ዶሮና ምስሩ
ወደታች ስንምሰው፣ ብዝበዛ ነው ሥሩ።

የርግማኑን ራስ፣ ሆድ ይዘን ተፈጥረን
መቸገር ሳያንስን
ለጠበቃ አልባዎች፣ ሸክም አሸጋግረን
ከጥንት እስከዛሬ
ጭንቅህን በልሳን፣ ተርጉመህ ባትነግረን
ይቅር በለን በሬ

አህያ ሆይ ማረን!!

## ንቀን ያለፍነው ቃል

ከለታት አንድ ቀን፣ ወደ ቤቷ ሄድኩኝ
ጥቅል ጎመን አርዳ፣ እንጉዳዩን ጠብሳ
ጋበዘችኝ ምሳ
ሙያዋን አደነቅሁ
ገበታው ሲነሳ
ካያቷ ተዋወቅሁ።

አረጋዊት ናቸው፣ አድሜያቸው የገፋ
ድሮ ልጅ እያሉ፣ አይናቸው የጠፋ
በድሜያቸው በረካ፣ በፅዋቻቸው ጭላጭ
አምሯቸው ብሩህ፣ ልሳናቸው ምላጭ
ወግ ማውጋት ጀመሩ
ቃል እያለዘቡ
ቃል እየጠረቡ፣ ቃል እያሳመሩ
ሀረግ አለዝበው፣ ዘይቤ እየነቀሱ
በጸጥታ ሞቶ፣ ያላጀብ ተቀብሮ
የተረሳ ታሪክ እየቀሰቀሱ
እንደ መቅረፀ ድምፅ፣ ጆሮየን ጠመድሁት
አጥብቆ ገረመኝ
ያረጋዊቷ ወግ፣ ቅድም ከበላሁት
ከንጉዳዩ ዝልዝል፣ የበለጠ ጣመኝ።

ጸሐፊ ትዛዛት ቻል ብለው ያለፉት
ዜና ነጋሪዎች፣ እይተው የገደፉት
ያገሬን ሰው ገድል፣ መከራ ፍስሐ
ሳልታከት ቀዳሁት፣ ልክ እንዳርብ ውሃ።

ከጥሞናየ ላይ ላፍታ ተፋትቼ
ጋባገቤን ፈለግኋት
ፊትለፊቴ አየኋት
ያቻት ያቻትና
ከሶፋው ላይ ሆና
አግሮቿን ዝርግትግት፣ ሰውነቷን ዘና
እንደፊት መስተዋት
ዘመናይ ሞባይሏን፣ ፊቷ ስር ደቅና
ከስልኳ ሰሌዳ፣ ፊደል ትነካለች
ፎቶ ታምሳለች፣ ኢሜል ትልካለች
ያያቷ ጣፋጭ ወግ፣ ላፍታ እንኳ መች ደንቋት
ሜሴንጀር ዋትሳፕ፣ ኢሞ ቴሌግራም
ሁሉን የወሬ ቋት
ትበረብራለች፣
......

ካሥር አመት በፊት
ለረፍት ከከተማ፣ ወደ ገጠር ሄጄ
ደጅ ላይ ማለዳ፣ ፀሐይ ስር ተጥጄ
አያቴ ብቅ ብሎ
ከተቀመጥሁበት የወይራ ግንድ ላይ፣ ራሱን አዳብሎ
"ያኔ ጎበዝ ሳለሁ" ብሎ ወግ ሲወጥን
አልባሌ ወሬ፣ እኔን የማይመጥን
የሰማሁ ይመስል፣ በጎይል አዛግቼ
ከካፖርቴ ኪስ ውስጥ፣ መጽሐፍ አውጥቼ
(የማርክስ፣ የፍሮይድ ምናልባት የኒቼ?)
ገለብ ገለጥ ሳደርግ፣ እሱ ይህን አይቶ
የጀመረውን ቃል፣ አንጠልጥሎ ትቶ
"ለጥናት ነው መስል፣ እዚህ መቀመጥህ፣
ወግድልኝ በለኝ፣ እንዳልበጠብጥህ"

ብሎ ይወገዳል
አድማጭ ካጣጭ ጋራ ወደሚገኝበት፣ ጠላ ቤት ይሄዳል።

አያቴ ከሞተ፣ አመታት አለፉ
ፀፀት ጭንቅላቴን፣ በብረት መዳፉ
እየኮረኮመኝ
ሀፍረት በሸኮናው፣ እየረመረመኝ
በራሴ ስበግን
ምን ሆኘ ነበር ግን

ምን ነኩቶኝ ነበር ግን?
በማለት አጥብቄ ራሴን ስረግም
ይሄውና ዛሬ
ጋባዤን አየኋት፣ ታሪኬን ስትደግም።

አንድም በመሰልቸት፣ አንድም በቻልታ
ወይ ባወቅሁሽ ናቅሁሽ፣ አለያም በወረት
የያዝነውን ዳቦ፣ ቆጥረነው ከኩረት
ጠላ ከሚጠጣ፣ ቆሎ ከሚበላ
አድፍ ከሚለብሰው
ለዐይን ከማይሞላ
ካንድ ስም አልባ ሰው
ምን ጥበብ ይገኛል? በሚል ተዘናግተን
በቻይና ቅፅር ጡብ፣ ጆሯችንን ዘግተን
ልቦና ቆልፈን
ንቀን ያለፍነው ቃል፣ ንቆ ነው ያለፈን።



## መሲታወት ፊት ቆሜ እንዲህ እላለሁ

"በለስ ፍሬ ባትሰጥ"፣ ሎሚ መሽተት ቢሳናት
ኤሊ ላባ ብትለብስ፣ ወፌን ድንጋይ ቢጫናት
ሰማይ እንዳለት ቢወቀር
ጊዜ ደከሞት ቆሞ ቢቀር
ጨረቃ አመድ ብትቅም
ፀሐይ ጥርሷን ብትለቅም

ስልጣኔን ነቀዝ በልቶት፣ ኦና ቢሆን አገር ምድሩ
ፒራሚዶች ባንድ ሌሊት፣ የኩበት ክምር ሆነው ቢያድሩ
ተፈጥሮ ለሕዝብ ቅነሳ
ሰው በሰው ላይ ብታስነሳ
አንዱ ካንዱ ቢተራረድ
ጠፈር በከል ቢጋረድ

ሙሴን ባሕር ቢበላው፣ የኖህ መርከብ ቢሰጥም
ሕይወት ምስጢር ባትገልጥም
የድል ድርሻየን ጥዋ፣ ጭላጭ ሳይቀር እስካጣጥም
የምሻውን እስከማገኝ፣ ለመሸነፍ እጅ አልሰጥም
እንኳን ተስፋ፣ ጢም አልቆርጥም።

## እኔ ምፈልገው

እውነት ለመናገር፣ እኔ ምፈልገው
ካንቺ ጋር መጋባት
ይህን ሐምሌ ፊቴን፣ ደጋግሞ ማራባት
ከወፎች ጋር መንቃት፣ በጊዜ ቤት መግባት።

"ምንም ድሃ ቢሆን፣ ባይኖረውም ሀብት
ከደጃፍ ሲቀመጥ፣ ደስ ይላል አባት"
ለሚል መናኛ ጥቅስ! ኑሮየን ማይመጥን።

ሲሻኝ በየባንኩ፣ ስፈልግ በሳጥን
የተረፈኝ ገንዘብ
ደጃፍ ላይ ቁጭ ብየ፣ ድሀ የምታዘብ
ተምሳሌትነቴ፣ የሚዳረስ ባለም
ሞዴል አባወራ፣ ተብየ ምሸለም
አገሬን ማስከበር
ሕዝቤን ማስተባበር
የልጅ ልጅ አፍርቼ
በመቶ አመት ሙቼ
ሥላሴ መቀበር
ምኞቴ ይህ ነበር።

እውነት ለመናገር፣ እኔ እምፈልገው
ወንደላጤ ኑሮ
በሴቶች መታጀብ፣ ልክ እንዳውራ ዶሮ
ጊዜ ጥሎኝ ቢሄድ፣ ቀን ቢገሰግስም
መላው ጭንቅላቴ፣ ገብስማ ቢለብስም
ላቅማዳም ነው እንጂ፣ ለትዳር አልደርስም።

ደሞ
ዘር መዝራት እርሜ ነው፣ ደጋግሜ ባርስም
ባለመኖር ላሉት፣ ሥቃይ አላወርስም



ቢፈልግ ሌላው ሕዝብ
ይፈልፍል እንደዝንብ
ይባዛ እንደንጉዳይ
አገር ሥራው ያውጣው! ሰው የራሱ ጉዳይ!!
የራሴ ፈጣሪ፣ ነኝ የራሴ ገዳይ!!

እኔ ምፈልገው...
እኔ ምፈልገው....
ምንድር ነው? ምንድነው?

---

ገንዘብ ቢመዘበር፣ በገንዘብ ይተካል
እድሜ ለጉልበትሽ፣ በላቡ ለሚያድር
በውርስ በስጦታ፣ ግፋ ቢል በብድር።

በቆጠብነው ቁጥር
ጊዜ ነው የሚያጥር
እድሜ ነው የሚያልቀው
የምንፈልገውን በቅጡ ሳናውቀው።

## ሰውረኝ!

እግዚአብሔር እረኛየ ነው
መከላከያ ሰራዊት በረኛየ ነው!
አቤቱ! እኔን ለቅድመ እርጅና ያጨህ
ስቴበን ሃውኪንስን፣ በሰባ ስድስት አመቱ የቀጨህ
የፊዚስቱ በረከት ይደርብን! በሌጋሲው አረስርሰን!
ለኔ ጭንቅላቱን ከነ እውቀት ጥማቱ
ለጠላቴ ዊልቸሩን ከነ ቁርጥማቱ
አውርሰን!

አቤቱ ሐጥያቴ ብዙ ነው፣ እውቃለሁ መቼም አትምረኝ
እኔም መንግሥት መሆን እንጂ፣ መንግሥተ ሰማያት አያምረኝ
ይልቅ ከነህ መቅሰፍቶች ሰውረኝ!

የዝኒፈር ሎፔዝን ዳሌ፣ እግርን አመሳቅሎ ከመመኘት
በፌዴራል ፖሊስ ፊት፣ እጅን አመሳቅሎ ከመገኘት!
የማእከላዊ ሙዝየምን፣ በመንፈቅ ሌሊት ከመጎብኘት
ባድማው ምክንያት፣ እንዲያው በደፈና
ከላይ ባድማ ተንታኞች፣ ከታች ባድማ በታኞች በታጠረ ጎዳና
ሰገራ ጭኖ ማለፍ ፈርቶ፣ ቤቴ በር ላይ ከቆመው ቦቲ መኪና

ሰውረኝ!

ከእኩለ ሌሊት ውሃ ጥም
ከፍቅሬ ቶሎሳ ግጥም

ሰውረኝ!

ባስራንድ ፐርሰንት ከሚያንስ አገር
ባስራንድ ፐርሰንት ከሚያድግ ጭገር

ሰውረኝ!

ሥራ ከፈታች የፌስቡክ መናኝ፣ ተቀዶ የሚሰፋ ቆብ የሌላት
ኔትወርክና ጊዜ የሞላት
ከዱባይም ይሁን ከዩናይትድ ስቴት
ላይቭ ጠምዳ ቀኑን ሙሉ ከምትዘበዝብ ባልቴት

ሰውረኝ!

ልክ እንደ ቅድሙ "አዝመራ ሽሮ" ቤት ገብቼ ለምሳ
ማጅራቴን ጨምድዶ ሰልፊ ከሚደፍቀኝ ጎረምሳ!

ሰውረኝ!

ብቻ ብቻ ወዘተ
ምን ይሳንሃል ላንተ!

## መወድስ ላርባ ምንጭ ከተማ

ሐመልማል ልቃቂት፣ አረንጓዴ ዝሃ
ሰማይ ሙሉ ቅጠል፣ ምድር ሙሉ ውሃ
የተራራሽ ሞገስ
መንበረ ጸባኦት
ላንቺ በሰገድኩኝ፣ አገር ቢሆን ጣኦት

ሚዘፍንልሽ ጠፍቶ
ሚቀኝልሽ ጠፍቶ
ይሄ ሁላ መልክሽ፣ የመናኝ ቁንጅና
አገር ባዝማሪ እንጂ፣ በንጉሥ አይቀና*።

---

*አይቀና የሚለው ቃል የመነጨው ከማቅናት ነው፣ (አገር መግዛት ማሰልጠን የሚል ትርጉም አለው።)



## ውጊያ ሲሆን ኑሮ

በጃን ሜዳ ሰማይ
ሎሚ ተወርውሮ፣ መቾ መሬት አረፈ
ከምእመናን አንዱ
“ኀበዝ ተገን ያዙ” አለና ለፈፈ
ጉድ ነው ከዚያ ወድያ
ሕዝባዳም ታመሰ
አጀቡ ፈረሰ።

ማታ፣
“አሳዛኝ ዜና
ዛሬ ጃንሜዳ በተባለው ሰፈር አቅራቢያ
በደረሰው የወከባና መረጋገጥ አደጋ ሳቢያ
.......”

ኑሮ ውጊያ ሲሆን፣ ውጊያ ሲሆን ኑሮ
ልክ እንደ እግዚአብሔር ፊት፣ ሰላም ተሰውሮ
መቶ ሰው ይገድላል፣ ሎሚ ተወርውሮ።

## ቢታነፅ ቢወቀር

እኔም አንድ ሰሞን
ልክ እንደ ሰሎሞን
"ሁሉም ከንቱ ከንቱ ነፋስን መከተል"
ሳይጥሉ መታገል፣ ሳይከብሩ መባተል
እያልሁ አጨልሜ
በራሴ ለግሜ
እፈላሰፍ ነበር።

ከዚያ አንቺን አገኘሁ
በጓሮ በር በኩል፣ ሰሎሞኔን ሸኘሁ
መፈጠሬን ወደድሁ
ነፋስ አሳድጂ
እንደ ቆቅ አጠመድሁ
ከፀሐይዋ በቻቻ፣ ግልገል ፀሐይ ፈጠርሁ
ለአናው አምፖሌ፣ ብርሃን አበደርሁ
ማቅ የነበረው ጨርቅ፣ ሸማ ሆኖ ቆየኝ
ከንቱ የነበረው፣ እንቱ ሆኖ ታየኝ።

ለካስ
ጠቢብ ቢያስተምረው፣ መከራ ቢመክረው
አካሉና ልቡ ቢታነፅ፣ ቢወቀር
ሰው አቅሙን አያውቅም፣ ካልወደደ በቀር።



## የመስኮት ዳር ምህላ

በባእድ አገር መኖር፣ የተራዘመ ሞት ፍርድ ነው
ብለው ሲሉኝ፣ እያለቀስኩ እስቃለሁ
ከሞት መታገል አውቃለሁ
ወደ ባሕር ስወረወር፣ አፀድ መሃል እወድቃለሁ።

ይሄ መስኮት ይመስከር
የመስታወት ሀውልት ሁኖ፣ ያሳለፍኩትን ይዘከር!
ይሄ ሁሉ መከራ
ይሄ ሁሉ የበረዶ ጭፍና
በኮቴው ደቅድቆኝ ያልፍና
ታሪኬን ለመንገር እቆያለሁ
የቅጠሎቼን ትንሣኤ አያለሁ!

## ለሕዝቡ ብሎ

ምነው ገለሌ
ምነው ገለሌ
አመሉ ቅጥፈት፣ ስሙም አገሌ
በከፊል መናኝ፣ ግማሽ ተጋዳይ
የማጀቱን ጉድ፣ የራሱን ጉዳይ
ከድኖ በማብሰል
ባገሩ ጣጣ፣ የሚብሰለሰል
ሰብከት በጉንጩ
የግሣፄና የርግማን ምንጩ።

ፍሬ ከርስኪው የማይጠገብ
ካልጋው አጠገብ
ዘብ ቆሞ አዳሪው
ቆሪጥ ወታደር
ተልኮው ጥሪው
በካሜራ ፊት ሲያወራ ማደር።

ቢያምር ባያምር፣ ቢጣፍጥ ባይጥም
ካሜራና ጅል፣ ትይንት አይመርጥም።

በቅሎ አትሽልሙት
ፈረስ አትጫኑ
ፈረስ እኮ ነው የገዛ ጭኑ
ካንደኛው ዜጋ ወዳንዱ ዜጋ
እየጋለበ
በሀሜት ዘገር በስድብ ሎጋ
እያካለበ
የሚዋደቅ ነው በየስክሪኑ

በላፕቶፑ ላይ ሰርክ ተጥዶ
አንድ ሺ ዘልፎ

አንድ ሺ አዋርዶ
ዘመን የጣላት
ዘመድ የጠላት
ባልቴት ይመስል
ስድብ ሲቀቅል
ነገር ሲያማስል
ሲያማርር ውሎ
ለሕዝቡ ብሎ

ካልጋው ተነስቶ ፍሪጁ ድረስ
ጊዜ እያጠረው አይንቀሳቀስ
ለሕዝቡ ብሎ።

## አይመንን አይጨምት

ጉብዝና ዘላን ነው፣ በመጣበት ሄደ
ጎፈሬ እንደ አቧራ
ነፋስ ተከትሎ
ካናት ተነጥሎ
ሩቅ ተሰደደ
ደረት ቆረፈደ
ትከሻ ተናደ
ተሸረሸረ አቅሙ
ጉልበትን በቁሙ
ስውር ነቀዝ በላው
ልብ ነው የደላው
ጊዜ ሄደ ብሎ
አቅሙን የማይገምት
እግርን ተከትሎ
አይመንን አይጨምት።



## በእቅፍሽ ውስጥ ያለው ሰላም

በደጃፌ
ያዱኛ ጅረት ይፈስሳል
ሲዘረጋ መዳፌ
እልማዝ እፍሶ ይመለሳል።

ድህነትን አልቀድስም፣ ሀብታም መሆን አልጠላም
ግና ገንዘብ ኪስን እንጂ፣ የልብን ክፍተት አይሞላም
ከሁሉም ግን የሚልቀው፣ እቅፍሽ ውስጥ ያለው ሰላም።

በጉልምስና ዘመኔ፣ ወደ ልጅነት ተዛውሬ
የወይን ፅዋየን ወርውሬ
እልፍ ጡቶችን ብጠባ
ካንዷት ሽንቁር ተመዝገቤ፣ ሌላይቱ ውስጥ ብገባ
ብለዋውጥ ማህደር
ብቀያይር ሰገባ
ምን አገኘሁ? ምን አተረፍሁ? ምን ፈየድኩኝ? ምኔ ረባ?

ሥጋ በሥጋ ቢሞረድ፣ የደነዘ ነፍስ አይሰላም
ከሁሉም ግን የሚልቀው፣ እቅፍሽ ውስጥ ያለው ሰላም።

## ሚሊዮን ፀሐዮች ሚሊዮን ጨለሞች

ጨረቃ ብቅ አለች፣ ፀሐይ ስትከስም
ያው እንደ ወትሮ ነው
የምሽት የንጋት፣ ፈረቃው አይፈርስም!

የኔ ግን ይለያል
ልቦናየ ቢማስ
ሚሊዮን ፀሐዮች፣ ሚሊዮን ጨለሞች!
ሺ ሰማይ፣ ሺህ አድማስ
ተገልጦ ይታያል።

ስንቴ በጽልሙቴ፣ ዙርያየን አዳፈንሁ
ስንቴ በጨረሬ፣ የምድርን ዐይን ወጋሁ
ባንድ ቀን ውስጥ ብቻ
ስንት ጊዜ መሸቼ፣ ስንት ጊዜ ነጋሁ!



## የውበት ጀርባው

አንተ እሚታይህ፣ የሚያምር ፈገግታ
ያበባ ጉትቻ
ላንተ እሚታይህ፣ ውብ ገጽታ ብቻ።

ጥርሷን ጉራማይሌ፣ የተነቀሰች ቀን
ያየቺው መከራ፣ ያየቺው ሰቀቀን
የጆሮዋን ጫፉን፣ በሾህ ስትበሳ
የበላችው ፍዳ፣ ያየቺው አበሳ
የዋጠችው ሕመም፣ ከሬት የመረረ
የቀመሰው ማነው፣ ከሷ በስተቀረ?

ከያንዳንዱ ታላቅ ውበት በስተጀርባ
ሲንዠቀዠቅ ኑሯል፣ ብዙ ደምና እንባ።

ይሄም ታላቅ ዜማ
ይሄም ታላቅ ሥዕል
ይሄም ታላቅ ተረት
ይሄም ታላቅ ድርሰት
ከፊትህ አልቆመም፣ እንደ መና ወርዶ
ሥቃይ ያቃልላል፣ ከሥቃይ ተወልዶ።

## ሀሳብ ከሐምሌ ጣራ ስር

ይህ ዝናብ
ይህ ርጥብ ሲሳይ
የሚወርደው ጣራዩ ላይ
በደጃፌ ጠኒያም አፈር፣ ተሰልቅጦ ይቀራል
ወይስ ጅረት ተፈናጦ፣ ያገር ድንበር ይሻገራል?

ይሄስ ፍቅር ፅኑ ነው ወይ? ከጊዜ ጋር የማያብር
መነሻው የልብሽ ፈቃድ፣ መዳረሻው መቃብር
ወይስ እንግዳ ባቡር፣ በባእድ የሚዘወር
ከፊት ካለው ፈርማታ ላይ፣ አንጠባጥቦኝ የሚሰወር?

ይብላኝ ለልቦናዩ
ጥያቄና ተስፋ እንጂ፣ ምላሽ ለማያፈልቀው
ብቻ …
እንደሚዘንብ ነው የማውቀው
እንደምወድሽ ነው የማውቀው።



## የጥቅምት መስከ ነኝ!!

ሰው ለሰው ይፈርዳል
ልብን ዘልቆ ሳያይ
ሳልቃሽ አያዝን
በፈካ ገጽ ውስጥ፣ ያደፈጠን ሥቃይ
ማነው የመዘነ?

የይስሙላም ይሁን፣ ከልብ ያለቀሰ
አያጣም አይዞህ ባይ
ካንጀት ይሁን ካንገት፣ እንባ ላፈሰሰ
አይጠፋም ከምንገድ፣ መሐረብ አቀባይ።

ይብላኝ ላሳሳች ፊት፣ አፅናኝ ለማይጋብዝ
አንዳንድ ሀዘን አለ
ከላይ ተሰውሮ፣ ልብ የሚበዘብዝ

የጥቅምት ብሩህ መስከ፣ አደይ የለበሰ
ስንቱን ጉድ አዝሎታል፣ ሥሩ ከተማሰ!!
የጥቅምት መስከ ነኝ፣ አደይ ያደመቀው
ፈገግታ ቢውጠው፣ ዘበት ቢደብቀው
የኔን ብቻ ሕመም፣ እኔው ነኝ የማውቀው።

(ተከፍተው የተከፉ ለማይመስሉ)

## ኖረሽ እይው ብቃ

ጨለማ ነህ ብለሽ፣ እኔን ስትተቺ
ዘልለሽ አትጠግቢ፣ ስቀሽ አትሰለቺ
ወርሀ-ጽጌ* ነው፣ አመት ሙሉ ላንቺ።

ደም በየቀኑ
ፋሲካ ነው ኑሮሽ
ያለም ሰቀቀኑ
ሩቅ ነው ሊጀሮሽ
ለፍጥረት ሰቆቃ
ለጋ ነው አእምሮሽ
ገላሽም ነው ጮርቃ
ሌላም አልልሽም፣ ኖረሽ እይው ብቃ።

በየጎዳናሽ ላይ፣ እደይ የሚያነጥፍ
በየዛፉ ቅርፊት፣ ስምሽን የሚጥፍ
በዝቶልሽ ፈልቶልሽ፣ አንቺን ሚያሽሞነሙን
ቀምሰሺው አታቂም፣ የብቻነት ሽክሙን።

እዎ

መፈቀር መታጀብ፣ ከኔከታር ይጥማል
ግን ደግሞ ይገጥማል
በተወደሱበት፣ እንደበት መነቀፍ
ውብ ገላ ጠብቆ፣ ርጥብ ንፋስ ማቀፍ

አንዳንዴ ይገጥማል
የማይሰምር ምኞት፣ የማያልቅ ጥበቃ
ሌላም አልልሽም፣ ኖረሽ እይው ብቃ።

አንቺ ደስታ ወዳጅ!!
በለምለም አፀድ ውስጥ፣ ቢራቢሮ አሳዳጅ
ኑሮ ምትታይሽ፣ እንደ ጣእስ* ቀልማ





እንዳትሸወጂ፣ ባዝማሪዎች ዜማ
በሸንጋዮች ቃላት
ሕይወትም እንደጃርት፣ የሾህ ቀሚስ አላት።

ተድላም ከሀዘን ጋር ያልፉል በፈረቃ
ከሣቅ በስተጀርባ፣ ይሰለፉል ሲቃ
ሌላም አልልሽም፣ ኖረሽ እይው ብቃ።

---

*ወርሀ ጽጌ (ያበባ ወር - Spring)
*ጣእስ (በሚያምር ህብረ ቀለማት የተዋበች ወፍ - Peacock)

## በሽንጎ ተጀንኘ

ፍቅሬን በግልፕ፣ ቢደባባይ
ደስታየን በድንጋይ ሰሌዳ ላይ
መናዘዜ
ቅሬታየን በደብዛዛ ርሳስ
መከራየን በለሆሳስ
ጭንቄን በምስጢር መያዜ
ካዘናጋሽ

አንድ ቁምነገር ላውጋሽ!
ተከፍቼ
ግና ፊቴ ላይ የብርሃን ዱቄት ነፍቼ
ምድር አትችለውን ችየ፣ ሆዴን ከጠረፍ አስፍቼ
ከሾህ አክሊሌ በላይ፣ ያልማገዝ ዘውዴን ደፍቼ
በሽንጎ ተጀንኘ፣ በእልፍኜ ብስለመለም
ሕመምን አለማወጅ፣ አልታመምኩም ማለት አይደለም።



## የተከፈተ በር

የቤታችን በሩ፣
ከፍተሽው እንደሄድሽ፣ ዛሬም አልተዘጋም
የነበረኝ የለም፣ ለቀማኛ አልሰጋም
እምቢ ካልሽ እምቢ ነው፣ ዕኑ ነው ያንች ቃል
እንደማትመለሽ፣ አእምሮየ ያውቃል።

ግን አልፈርድበትም፣ ልቤ ቢያመነታ
ምኞት በሞላው ቤት፣ እውቀት የለው ቦታ።

ተስፋ አይቆርጥም ደግሞ
ልቤ ሀልሙን ያምናል
ይለኛል ደጋግሞ፣
"ትመለስ ይሆናል
ትመለስ ይሆናል
ትመለስ ይሆናል።"

እኔም በምላሹ፣ ልቤን ፊት ሳልሰጠው
እንዲህ እለዋለሁ፣ ተስፋ ላስቆርጠው
"ጠጠር ላይቀቀል፣ አልማገዝ ላይከለስ
በደመና ራስጌ፣ ጎጆ ላይቀለስ
እኔም አልሻሻል፣ እሷም አትመለስ።

ሰማይ ሰም ይመስል፣ ቢንጠባጠብ ቀልጦ
የረር ፈልሶ ቢሸሽ፣ ቢከተል እንጦጦ
ባሕሮች ቢከስሙ፣ ምድር ብትናወጥ
እሷም አትመለስ፣ እኔም አልለወጥ።

በዙሪያየ ያለው ጸጋ ብዙ ነበር
ግና ከንፍ አብቅሎ
ፍቅርሽ ጥሎኝ ሲበር
ከኔ ጋር የቀረው
የተቆለፈ ልብ፣ የተከፈተ በር።

## የሌት ማህሌት

ትንሽ ቆየት ብሎ
ኮረንቲው ይጠፋል
እሱን ተከትሎ
ደምኖ ያካፋል
ከናፍቆትሽ በቀር፣ ሁሉ ነገር ያልፋል።

አሁን መብራት ጠፋ፣ ተረኛ ነን አይደል
ቁና ይገፈ ቀረብሁ፣ ጨለማ ሲታደል።

እያገላበጠ ብቻነት አመሰኝ
"ዝናቡ እየጣለ ጋራ ጋራውን
ጎርፍ ያመጣሽ እንደሁ ልጠብቅ ወንዙን"
የሚል እንጉርጉሮ በድንገት ታወሰኝ
ግን ይሄ ትውስታ
አራራይ ትዝታ
ለቆሰለው ልቤ፣ መዳኒት አልሆነም
ያባቶቼ ዘፈን፣ ለኔ አልተዘፈነም።

ማዶ ዝናብ ዘንቧል
ዶፉን ተከናንቧል
እንጦጦ ዲልዲላ
በገፈጅ ይመስል፣ ቀበናም ቢሞላ
ምንም አያመጣ፣ ከእድፍ ውሃ ሌላ።

እሳት ነው ፍጥረትሽ፣ ከውሃ ጋ አትኖሪም
አንቺ መብረቅ እንጂ፣ ጎርፍ አትሳፈሪም።



## ከምነቴ ጋር ቀረሁ

አውቃለሁ!
አታምኝም በማምነው
ያንደኛው ሰው መንገድ፣ ለሌላው ገደል ነው።
ቢቀና ጎዳናው፣ ቢወለወል አስፋልት
አብሮ ከማያልም፣ አብሮ መሄድ ልፋት
ያንደኛው ሰው እግር፣ ለሌላው እንቅፋት።

ባልጮህ ባደባባይ
ምኩራብ ባልገነባ፣ መዝሙር ባላሰማ
ከጥላየ በቀር፣ ባይኖረኝ ተከታይ
በቃል ወይ በዜማ
ተገልጦ ባይታይ
በልብ ተጠንስሶ፣ ባይን የሚገነፍል
እኔም እምነት አለኝ፣ ዋጋ የሚያስከፍል።

"እምነት - ተስፋ - ፍቅር"
መቸ ባንድ ላይ ሁኖ
ለሰው ልጅ ይሰጣል
በምነቱ የፀና፣ ድንገት ፍቅሩን ያጣል
ፍቅርሽን ሽኝቼው፣ ተስፋየን አባረርሁ
ከምነቴ ጋር ቀረሁ።

## ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ

የድሜ ነፋስ በገላየ ተረማምዶ ኮበለለ
ልቤን ከንዴን እያዛለ
ያቀፍኩትን እየቀማ፣ የያዝኩትን እያስጣለ።

እድል በኔ ጨከነ ስል፣ በምረት እጅ ደባበሰኝ
አንቺን ነጥቆ ከቅፌ ላይ፣ በትውስታ ደሞ ካሰኝ።

አስታወሰኝ
አስታወሰኝ

ወድያው ታይቶ፣ ጠፊ ኩርፍያሽ
ገራም ሳቅሽ፣ ልዝብ ልፍያሽ
ያለም ዘፋኝ የማያውቀው
የግልሽ ዳንስ ውዝዋዜ
ትውስ ትውስ ባለኝ ጊዜ
ከግር ጥፍሬ
እስከ ጠጉሬ
ደስታ ነው የሚያቀልመኝ
ያንቺን ነገር ባሰብሁ ቁጥር፣ ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ።

በሰጠሽኝ ጸጋ መጠን፣ የሰራሽኝ ጉድ አያልቅም
እኔ ባንች ትዝታ እንጂ፣ በተራቢ ቀልድ አልስቅም
ማፍቀር ማለት ለካ ፍቺው፣ መጃጃል ነው አውቆ ፈቅዶ
ከገደል ላይ መወርወር ነው፣ ተጨፍኖ በራስ ፈርዶ።

አፈቀርኩሽ በየቀኑ፣ ተጃጃልሁኝ ደጋግሜ
ከገደል ላይ ተከሰከሼ፣ ሞተ ሲሉኝ አገግሜ
ያጥንቶቼን ርጋፊ፣ እንደዛጎል ለቃቅሜ
እንደ ቆሎ፣ ጥርሴን ቅሜ
ያደረኩሽ ሲደንቀኝ፣ ያደረግሺኝ ሲገርመኝ
እፍረት ፀፀት አይደለም፣ ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ!

አውቃለሁኝ ጊዜ ሂዷል፣ ታሪካችን ተጠቅልሏል።
በሄድንበት ጎዳና ላይ፣ የመለየት ዝናብ ጥሏል
በርምጃችን ምልክት ላይ፣ ረጃጅም ሰርዶ በቅሏል
ብቻ ሙሾ ቢደረደር፣ የሆነውን ላይለውጠው
ለንባየማ ፊት አልሰጠው።

ያሳሳምሽ ለዛ ቀርቶ፣ እንደ እንጎቻ እሚጥመኝ
የነከሽኝ የቧጨርሽኝ፣ አገርሽቶ ቁስሉ ሲያመኝ

ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ!!

## ገላ መንገደኛ

ገላ መንገደኛ፣ በመሸበት ያድራል
ሲመቸው ተሻግሮ፣ አዲስ ቤት ይሰራል
ልብ ነው ቋሚ-ቀር
እንደ ጥንቱ አይሰላም፣ የለመደው ሲቀር።



## ላንዲት ድንጋይ ፈላጭ አረጋዊት

እንዲት አረጋዊት
ጥቁር ኢትዮጵያዊት
ትመካበት የላት
ባለጸጋ ዘመድ
ፊቷ የለበሰ፣ ፅናት ላብና አመድ
እሷ አለቃ ሆና፣ ከንዶቿን ቀጣሪ
እሷ ድሃ ሆና፣ የሀብታሞች ጧሪ።

እየተጋች እድራ፣ እየለፋች ስትውል
እድሜና ተስፋዋን፣ ያስተሳሰረው ውል
ቢቀጥን ቢሳሳ
ከሽረሪት ፈትል
መሐረብ ዘርግታ
ተዘከሩኝ ሳትል
እንባ ሳታስቀድም
ምሬት ሳታስከትል

ፍላጎት ባይኖራት፣ ለውዳሴ ከንቱ
የሰራችው ገድል፣ ዜናው ባይሰማ
ይህ ሁሉ ከተማ
ህንጻው ስገነቱ
የሷን ላብ ጠብቶ ነው፣ የፋፋው ደረቱ።

እንዲት አረጋዊት
ጥቁር ኢትዮጵያዊት
በዝምታ ዜማ፣ ፅናት የምትዘምር
ደፈልቃል ከጆቿ፣ እፁብ ድንቅ ተአምር!
መዶሻው ተነሳ
እጇሬው በነነ
በመዳፎቿ ስር፣ ድንጋይ ዳቦ ሆነ!

# (የቀሳ* ግጥሞች)

*"ቀሳ" (ብቻ ብቻነት፣ ልዩነት፣ ፈረንጆች ካራንቴን የሚሉት)

"ቀሳ ወጣ" (ከቤት ወደ ዱር ኼደ፣ ብቻን ተቀመጠ፣ ተኛ ታመመ፣ ከቤተሰቡ ተለየ፣ የሚጋባ በሽታ ተስቦ ስለያዘው።)

ደስታ ተከለወልድ፣ _ዐዲስ መዝገበ ቃላት_፣ 1962 ዓ.ም ገጽ 1019።

## እንደምትወዳት ንገራት!

ሕይወት - የብድር በሬ፣ መቼ ሁሌ ይጠመዳል?
ለጊዜው ብቻ የመጣ፣ ጊዜው ሲደርስ ይሄዳል
የተሰጠህ ጸጋ ሁሉ፣ ደሞ ካንተ ይወሰዳል።

ቀለበት፣ አምባር አይደሉም
እጅህ ላይ፣ ሁል ጊዜ የሉም
ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት
ዛሬውኑ፣ አሁኑኑ፣ እንደምትወዳት ንገራት።

አበቦች ሁሉ ሳይረግፉ
ምዑዝ ሽታዎች ሳይጠፉ
ያፀድ በሮች ሳይቆለፉ
በንቦች ጎዳና ላይ፣ ተርቦች ሳይሰለፉ
በንፉስ ክንፍ ሳይመታ
ሕይወት - የላምባ መብራት
አሁኑኑ ዛሬውኑ፣ እንደምትወዳት ንገራት።

ርቃ ሳትገሰግስ
ገና ስንቋን ስትደግስ
እንዲሁ እንዳማረባት
ቀልብህ እንደቀረባት
መቃብር በመዳፉ
እንደ ጠጠር ሳይቀልባት
አፈሩን ሳትዛመድ
ወደ እማትቀባው አመድ
ወደ እማትስበው አየር
ሳትቀየር
አንተም እንደበት ሳለህ፣ እሷም ጆሮ ሳያጥራት
ዛሬውኑ! አሁኑኑ! እንደምትወዳት ንገራት!!

## ግጥሎት (ግጥምና ጠሎት)

አቤቱ ውሃን አየር ላይ ያረጋህ
ምድሪቱን በጠረባ የዘረጋህ
በጃርት ወስፌ ጠንቁለህ፣ ያሞራን ዐይን ያፈሰስህ
ካላጣኸው እጄጠባብ፣ ኤሊን ድንጊያ ያለበስህ
ካልቸገረህ ወጣትነት፣ አዳምን ባርባ አመት ያስረጀህ
በኅዳር በሽታ ዘመዶቼን የፈጀህ።

እንደምን ዝም ትላለህ፣ በቫይረስ ሲቀቀል ዓለም
በሰማይ ቤት እፍረት የለም?
ደሞ ተከታዮችህ ሁሉ
ከየጎሬው እየፈሉ
ቁጣው ነው መቅሠፍት ያመጣ እያሉ
ጆሯችንን በመጽሐፈ ባልቴት፣ ኪሳቸውን በመባ ይሞላሉ።

ግን ምንድነው የሚያስቆጣህ
ጸሎት አልጎደለብህ፣ ምስጋና ውዳሴ አላጣህ
ደሞ እንኳን ኮሚኒስት ቻይና፣ መላው ዓለም በሞላ
እንኳንስ የሌሊት ወፍ፣ ሌቱን ጠቅልሎ ቢበላ
ለምን ይደብርሃል፣ አፒታይት ከሰጠኸው በኋላ
ያወላገድከው ቢጠለፍ፣ ያጣመምከው ቢሰበር
ውሉን ስቶ ቢመናቀር
ማነው ተጠያቂው ባክህ፣ ካንተና ካንተ በቀር።





እና ዛሬ ላይ አልጋየ ላይ፣ ተዳከሜ ተኝቼ
አልጋ ተቆራኝቼ
እንደ ኢዮብ እከክ ለብሼ፣ ተመስጌን እያልኩ እንድቀኝ
ፈገግ ብለህ ስትጠብቀኝ
እስኪበቃኝ ረግሜህ
እስከጠግብ አማርሬህ
እንደ ኢዮብ ሚስት፣ ልክ ልክህን ነግሬህ
ወደ ሌለህበት ዞሬ፣ ለዘላለም እተኛለሁ
ሥጋየን አራግፌ፣ እረፍቴን አገኛለሁ።

ድንገት ዘወር ብየ፣ ያለፈውን ስቃኝ
የመስከ ውሃ ነበርሁ፣ ሜዳ የማይበቃኝ
አሁን ግን ታሰርኩኝ፣ ባንድ ትልቅ ቀፎ።

ያንችም ነፃ ገላ
በትንሽ ሰቀላ
ቀረ ተቆልፎ
ለሌሎች የመጣው፣ ለኔናቺ ተርፎ።

ይሄ ግዙፍ መአት
ጠልፎ ሳያስቀረን
ማታ፣ ሁለት ሰአት
ቀጠሮ ነበረን

ትመጫለሽ ማታ?
ቀፎየን ልበርግድ፣ ሰንሰሉቴን ልፍታ?
ይነጠፍ ወይ አልጋው
ለኔ - ላንቺ - ለሞት
ሶስትዮሽ ምኝታ
ሶስትዮሽ ጨዋታ?

ይሰረዝ ቀጠሮው?
ወደ ፊት ይዛወር
ወደ ማናውቀው ቀን፣ ወደ ማናውቀው ወር?

አሁን እዚህ ሆነን፣ ቅንጦት ነው መገመት
እናስተላልፈው ወይ፣
ከለታት ላንዱ ቀን፣ ካመቶች ላንዱ ዓመት?

እንዳማረኝ ይቅር?
ያ ሙቀት! ያ ፍቅር!
ያ መስህብ፣ ያ ለዛ
ያ ተረከዝ! ያ ባት!
ናፍቆትም ደዌ ነው፣ የሌለው ከትባት።

## ሰው ከቀየው እንጂ

ወጥቼ ከቀሳው
ለጊዜው ታግየ
ሞትን ድል ብነሳው
መኖር አሸነፈኝ
ቤቴ ተደፍቶብኝ፣ ሁለት ወር አለፈኝ።

ተፈጥሮየ ከዳኝ፣ ፈሊጡን ቀየረ
አካሌ ሸፈተ፣ አዲስ ወግ ተማረ
ገላየ በቁሙ፣ ሳር ማብቀል ጀመረ።

እንዳልቆይ መታከት፣ እንዳልወጣ ሽብር
ሳይደከመኝ ተኝቼ
እንቅልፍ አንገቴ ላይ፣ ቀንበሩን ሳይሰብር
ካልጋ ተነስቼ
እየተደናገርሁ
እየተደናበርሁ
በምሳ ሰአቴ፣ ራት እየጋገርሁ
ኑሮ እንደ ሳር ጉንጉን፣ እያደናቀፈኝ
ሁለት ወር አለፈኝ!

ዛሬ ኮበለለ
ትላንትናን ቀድሞት፣ ባምባላይ ፈረሱ
ቀኔና ሌሊቴም፣ ሰልፍ እያፈረሱ
ይተራመሳሉ
ይርመሰመሳሉ

አርባም እድሜ ሆና
ያችን ለማሳጠር
ነፋስ በሰው ሲያድም፣ ከሞት ሲመሳጠር

ወዴትስ ይኬዳል
ሰው ከቀየው እንጂ፣ ካለም ይሰደዳል?

## ፀደይን በመስኮት

ከረምቱ ሲወጣ
ርጥብ ዳሱን ነቅሎ
አዳሜ
ከተሜ
ጃንጥላውን ሰቅሎ
ካቦርታውን ጥሎ።

አዳም ከሄዋኑ
(ድስት ከነክዳኑ)
ላጤውም ለብቻው
ወንዱ ደረት ሊያሳይ
በባሕር ዳርቻው
ሴቱም እንደልቡ፣ ቂጡን እየጣለ
በሙቅ አሸዋ ላይ
እየተንጋለለ
ቅብጠት ድርያ ሲያምረው
ማግጮድ ታጥቆ ገባ
ሁሉን የማይምረው
ፊት ያለውን ሁሉ
በብረት መዳፉ፣ የሚያጠናግረው።

እምቢልታ ተነፋ
ደወል ተደወለ
ያልታደለው ጠፋ
ቀሪው እቤት ዋለ
ሰው ቤቱ መሽገ
መስኮት እንደጋሻ፣ እየወለወለ።

በየአደባባዩ
እዩኝ እዩኝ ባዩ
እንዳልተጀነነ
ሰው ለመኖር ብሎ፣ ከኑሮ መነነ!

እኔም እንዳገሬው፣ ለነፍሴ ብሳሳ
ለብቻት ሰነበትኩ፣ ቤቴን እንደገሳ።

እምና እንዳልነበርኩኝ
የተፈጥሮ ሚዜ፣ የጸጋው ተካፋይ
የአልፍኝ እስረኛ ነኝ፣ አጮልቄ የማይ
ያውና አዚያ ማዶ፣ ጥርት ያለ ሰማይ
ያቻት አዚያ ማዶ፣ ያልተሞቀች ፀሐይ!

በየልምላሜው
በየዛፍ ቅጠሉ
ንቡ ወፉ ትሉ
ሲቦርቅ ሲራኮት!
እኔ ግን ሸኘሁት! ፀደይን በመስኮት።

## ኢይቆምም ዘፈኑ

የመከራ ሰርዶ
የመከራ ተክል
አንድ ርምጃ ሲሳብ፣ አምሳ መሰናክል
ሲገጥመው የኖረ
ጨርሶ መከሰምን፣ በትግሉ የሻረ
ሰው የፍጥረት ቁንጮ፣ የተሰጥዖ ሀብታም
እንደ ያሬድ ትል ነው፣ ጨርሶ አይረታም።

ቢወድቅ፣ ከንብል ቢል
ከዘመን መዳፍ ላይ
መች ሊፈርጥ እንደ እንቧይ
እድሜውስ መች አጥሮ
በተስፋ ገንትሮ
በኑሮ ጠጥሮ
ይነሳል ከምድር፣ እንደ ጎማ ነጥሮ።

የሞት ቀንዳም ፈረስ
ላዩ ላይ ቢሰግር
ለያንዳንዱ ጣጣ
ብልሀት ቢቸግር
መፍትሔ ቢታጣ
ደም ሲደርስ ቀኑ
ለተዘጉ በሮች
መበርገኛ ቁልፎች
ግልጥልጥ ይላሉ፣ ዛሬ ቢዳፈኑ
ባንቀልባ ይተካል፣ የዛሬው ከፈኑ
ሕይወት ማህሌታይ
ቴፑ ተሰባብሮም፣ አይቆምም ዘፈኑ።



## ለልደቴ፣

አጣ ፈንታ
ባልመረጥሁት ዘመን፣ ባልመረጥኩት ቦታ
ጎዳና ላይ አውጥቶኝ
እንቅፋት በየርምጃው፣ ተለክቶ ተሰጥቶኝ
ሲሻኝ እየሸሸሁ፣ ሲሻኝ እየተዋጋሁ
እንቅፋቴን በባዶ እግሬ፣ እንደ እንቧይ እየለጋሁ
ሕመምን እየሸወድኩ፣ ሞትን እያዘናጋሁ።

መኖር ሳልጠላ
ግና ለመኖር ብየ፣ የግብር እንጀራን ሳልበላ
አሜን የሚል ቃል ሳይወጣኝ
በጌቶች ፊት በፍርሃት፣ ጎንበስ ጎንበስ ሳያቃጣኝ
ነፃነቴን ከጥልቁ ሥር፣ እንደ ብርቅ አሳ አስግሬ

ያሻኝን ተናግሬ
ተጨብጭቦልኝ
አንዳንዴም ተወግሬ
ያለ አጀብ ያለጋሻ ጃግሬ
ባሻኝ እየገሰገስኩ
እንደ ወፍ በነፃነት፣ አገር ምድሩን እያዳረስኩ

በመረጥሁት ዛፍ ስር ተኝቼ
በጅሎች ካብ ስር ሸንቼ
እያወጋሁ፣ እየገጠምኩ፣ እያለመጥሁ፣ እያላገጥሁ
እንባዎቼን በቃል ምትሐት፣ ወደ ሣቅ እየለወጥሁ።
እየጣልኩ እየወደቅሁ፣ እየማቀቅሁ እየደላኝ
እነሆ አርባ አመት ሞላኝ!

## የዘንድሮ ነገር

ሟችን ባጀብ መቅበር
ተከልክሎ ባገር
የዘንድሮ ነገር
ተጎልቶ መድከም
ሀዘንን እንደ ዘውድ ለብቻ መሸከም!

በየሰው ጉንጭ ላይ፣ እንባ ቀልጦ እንደ ሰም
ደረት ሳይጎሰም
ፍታት ሳይፈታ
ያለ ምንም ሙሾ፣ ያለምን ዋይታ
ብቻየን ቀብር ዋልሁ
ከእድሜዬ መካከል፣ አንድ ዓመቴ ሞታ።

## አብርሃም፣ በግ፣ ይስሐቅ

እምጉመደ ሰብእ ይኄይስ ዘመደ እንስሳ
ወፍቅረ እንስሳ የዐቢ እምተፋቅሮ ሰብእ ለለጊዜሁ
እንዘ ገቶዊሁ ለይስሐቅ አደ አብርሃም አቡሁ
በግዕ እኮኑ ለይስሐቅ ቤዛሁ
ወበሙ ኢይትረፍ እምኃሊሁ
እበሳሰሃ ሰቀሉ አይሁድ አገዞግዚሁ።

መምህር ገብረ ሥላሴ ከንቶ (ዘኤልያስ)

(ውርስ ትርጉም)

ምን ሊፈይድ ምን ሊረባ፣ የዘር ሀረግ የደም ገመድ
ከሰው ልጆች ዝምድና፣ ይሻላል የእንስሳ ዘመድ
ፍቅርም በጊዜ ሚዛን ላይ ቢጣል
ከሰው ፍቅር፣ የእንስሳት ፍቅር ይበልጣል
አብርሃም እጅ ያለች ቢላ፣ በይስሐቅ ላይ ተመዝዛ
ከበግ በቀር ማን ነበረ፣ ለይስሐቅ የሆነ ቤዛ?
ደሞም አምሳያው፣ እንዳይተርፍ በምድሩ
ኢየሱስን የሰቀሉት፣ ዘመዶቹ ነበሩ።

## Uumama biraan ta'a!

"Ani si'iif nan du'a"
Jedhee siif hin kakadhu
Afaanuma mataa koon'
Du'a ofitti hin waammadhu!
Yeroos ni yaadattaa?
"Ittiin of ajjeesi" jettee
Barakiinaa yeroo natti ergite?
Ani yooman jiileree
Summii naaf ergite jedhee
Galata ergaa kee sanaa
Shamizii koon miiccadhe!
Rakkataa onnee kootii
Kan bal'atu hamma ardii
Kuurfaa'anii guutanis
Dhiphinnii baay'eefi gaddi
"Utuu naa darbee" malee
Ani "Utuun darbee" hin jedhu
Siree gubbaatii malee
Fooqiirraa kufuu hin fedhu.
Dooktariin dogoggoraan
Na kafanuus barbaadu
Akkuma dhaabbii kootti
Saanduqas natti qadaadu,
Aara caalaan qal'adha
Karaan ba'u hin dhabu
Biyya Waynii fi daadhiin jirutti ani rasaasa dhuguuf
Homaa sababa hin qabu!
Barri anaaf kenname
Yoo dhumateera ta'e
Guyyaan namummaa kootii
Xumurrisaa yoo ga'e
Ayyaanaafi waadaa haaraatiin
Gootee ana haa uumtu
Foddaa kee gubbaa teessee
Dimbiixii faarfachaa ooltu.
Dinbiixii ta'ee yoo xiqqaate
Qalbii kan keen dhuunfadha
Jiraadhee siinin arge;
Du'ee maalin buufadha?

ከአማርኛ ትርጉም Leta Kenei Aga

## የበሻህውረድ የፍጻሜ ቃል

እናንት ወታደሮች!
ጭፍሮች!
ባንዶች!
የገዳይ ስኳድ ጓዶች።
ገልን ምዩዚየም ውስጥ የምታኖሩ
ገላን ግን የምትሰብሩ
ጉዶች!

እነሆ ለፈቃዳችሁ
ከመገዛት አምልጬ
በባርነት ከመኖር
በነፃነት መሞትን መርጬ
ባፈሙዛችሁ ፊት ለፊት
ደረቴን እንደ መጽሐፍ ገልጬ
ሞት በጣቶቻችሁ መካከል
እንደ አሎሎ ሲለጋ፣
ተቻኩዬ ልቀልበው ነው
እንደጥምቀት ሎሚ፣ በጸጋ።

በርግጥ
በርግጥ መልካም ነው
በድሜ መቆየት፣ መዝለቅ
የነገን ጀንበር መናፈቅ
የከርሞን ምጽአት መጠበቅ
ያልተደረሰ ዜማን መስማት
ያልፈለቀ ወንዝ መጠማት
የህልምን ደሴት መውረር
ተስፋን እንደቢራቢሮ ማባረር፣
መልካም ነው!

ግና! ግና!
ባንዲራ ተዘርጥጦ
ከጠላት ጫማ ስር ሲጣል
አሜን ብሎ ከመኖር፣
እምቢ ብሎ ሞት ይመረጣል።

ጤዛ ምታከል እዱኛን
በእፍላ ምላስ አጣጥሞ
የዘላለም የቤት ሥራን
በመንፈቅ እድሜ ፈጥሞ
መሄድ! መውጣት! እየተቻለ
ማነው መኖር ማርጀት ነው ያለ?

እናንት ወታደሮች!
ጭፍሮች!
ባንዶች!
የገዳይ ስኳድ ጓዶች።
ገልን ምዩዚየም ውስጥ የምታኖሩ
ገላን.ግን የምትሰብሩ
ጉዶች!

አባቶቻችን ኢድዋ ላይ
የነብር ለምድ ለብሰው
በራሳቸው ላይ
ያንበሳ ጎፈር ነስንሰው
ባውሬ ጭምብል ቢፋለሙም
ልባቸው ግን ነበር የሰው።
የቂምን ድንበር የተሻገሩ
የጠላቶቻቸውን አስከሬን
አስቀድሰው የቀበሩ
የጨዋ ጨዋዎች ነበሩ።

ካርባ ዘመን በኋላ
ተለውጦ ዕድል ፈንታ፣
ጉልበታችን ተመናምኖ

ጉልበታችሁ ሲበረታ
ዘንግ የጨበጠ ፋኖ
በብረት አሞራ ሲረታ

የወፍ ጫጩትን፣ ገድሎ እንደሚፎክር ወስላታ
ብልግናችሁን እንደድል
ነውራችሁን እንደገድል፣
እንደክብር ተቆጥሮ
ይሉኝታና ሰብአዊነት
እንደጉድፍ ተሸቀንጥሮ
"እግዚኦ! ሥልጣኔ! እግዚኦ የሰው ተፈጥሮ!"
የሚያሰኝ ግፍ ስትሰሩ
የቂም ሀውልት ስታኖሩ
ኧረ ምን አላችሁ ዓለሙ? ምን አላችሁ እግዜሩ?

እሬሳችን በየጥሻው!
እንደጥቢ ቅጠል ተዘርቶ
ሙት አስነሺ መሲሕ ቀርቶ
ሙት ቀባሪ ዘመድ ጠፍቶ!
የገላችን ዕጣ ፈንታ
የጅብ ድግስ
ያሞራ ቁርስ
ያጥንታችን መዳረሻ
ያራዊት ሆድ ያራዊት ጥርስ
ይሄ ነው የናንተ ስጦታ?
ይሄ ነው የናንተ ውርስ?

ማይክላንጀሎ በሸራ
በቫቲካን መቅደስ ጣራ
አከፋፍቶ እንደሳለው
ወይም የኛ ሰባኪ
"እሳቱ የማይጠፋ!"
"ትሉ የማያንቀላፋ" እንደሚለው
ያለ የሲኦል ጨለማ
የሲኦል ከተማ



ወደ ምድር በማውረድ
ባለነጭ ባንዲራውን፣ ማርኮ በስለት ማረድ
መሠልጠን ነው መደንቆር?
መከበር ነው ወይስ መዋረድ?

እናንት ወታደሮች!
ጭፍሮች!
ባንዶች!
የገዳይ ስኳድ ጓዶች።
ገልን ምዩዚየም ውስጥ የምታኖሩ
ገላን ግን የምትሰብሩ
ጉዶች!

ወዳገሬ መጥታችሁ
አያችሁ!
ደነፋችሁ
የመርዝ ፍሊት ነፋችሁ!
እንደድራጎን እሳት ተፋችሁ።
በቆሣር ካባ
በብሩተስ ሰይፋችሁ
በግፍ አሸነፋችሁ!
ከምድረ ገጽ ጠረጋችሁ።
ምድረ ገጹ ይስፋችሁ!

ታድያ ትላንትና
በመጨረሻ ሌሊቴ
በመጨረሻ ውድቅቴ
የመጨረሻ ጥያቄ ከተፍ አለ ከፊቴ
የግዜር ድንቅ መዳፍ
ጨረቃን ከብርሃን ዛፍ
አሳምሮ የጠረበ

ምድርን በሐመልማል ምንጣፍ
ካድማስ እድማስ ያስዋበ
ዠንብን

ጉድፍን
መከራን
ለምን ዓላማ ሰራ?
ዳንቴን ያፈራ ማሕፀን
ሙሶሎኒን እንዴት አፈራ?

---

በሻህውረድ ሀብተወልድ በሁለተኛው የኢትዮ-ጣልያን ጦርነት ወቅት የታወቀ ኢትዮጵያዊ ምሁርና ፀረ-ፋሺስት አርበኛ ነበር። በሻህውረድ የኢኮኖሚክስ እና ንግድ ትምህርቱን በ1910ዎቹ ጀምሮ በአሜሪካ ተከታትሎ ወደ አገሩ ሲመለስ መጀመሪያ በድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት ዳይሬክተር፣ ከዚያም በአዲስ አበባ የገንዘብ ሚኒስቴር ዳይሬክተር ሆኖ አገልግሏል። በ1929 ዓመተ ምሕረት ግራዚያኒን ለመግደል በተደረገው ሙከራ ሴራ ውስጥ ተሳትፈሃል ተብሎ በቁጥጥር ስር ውሎ በጠላቶቹ እጅ ፍዳውን ከተቀበለ በኋላ ተገድሏል። መነባነቡ እሱንና መሰል አርበኞችን ለመዘከር የተደረሰ ሲሆን (October 2014) የኒውዮርክ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው "የጣልያኖች ውርስ በኢትዮጵያ" በተሰኘ ዝግጅት ላይ ቀርቧል!

## መውጫ

ሰውን ሰው ያደረገው ቋንቋ ነው። በሌላው በሌላውማ ከእንስሳት አይለይም። ጉንዳንና ንብም መንግሥት አላቸው። ዝንጀሮዎች የማህበር ባለቤት ናቸው። ፍልፈልም እርሻን ያውቃል።

ግጥም በጣም የተጣራ ቋንቋ ነው። በተርታ ንግግርና በግጥም መካከል ያለው ልዩነት በጥሬ ጥጥ እና በሸማ መካከል ያለውን ልዩነት ይመስላል።

ስለ ግጥም ከዚህ በፊት ደጋግሜ ስላወጋሁ፣ አሁን በፍቅር ግጥም ላይ አወሰናለሁ።

አንዳንዴ የነገሥታትን ዜና መዋዕል ገለጥ ገለጥ አድርጌ ስመለከት አንድ ጥያቄ ወደ ሀሳቤ ይመላለሳል። ስለ ወንድ እና ሴት ፍቅር የተገጠሙ ግጥሞች የቀረርቶና የሙሾ ግጥሞችን ያክል ያልተመዘገቡት ለምንድነው?! ጥንታዊ አዝማሪዎች ስለ ፍቅር አይዘፍኑም ነበር ማለት ነው? ለዚህ ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ የሚያቀርብልኝ እስካገኝ ድረስ የማወቅ ጉጉቴን በሚከተለው ግምቴ አስታገስኩት።

ታሪክ የመዝጋቢው ምርጫ ውጤት ነው። በርግጥ መዝጋቢውም ቢሆን ከበላዩ አዛዥና ተቆጣጣሪ ጌታ ስላለበት ሰፊ ነፃነት የለውም። የየዘመኑ ጌታ ላገዛዜ ይጠቅመኛል ለማህበረሰቤ ደህንነትና ህልውናም በጎ አስተዋፅኦ አለው ብሎ የሚያምንበትን ብቻ ነው ማስተላለፍ የሚፈቅደው። ለጌቶችም ሆነ ለገባሮች ህልውና ፋይዳ አላቸው ተብለው የሚገመቱ ነገሮች ሥራ፣ ትዳር፣ ጦርነት እና ሃይማኖት ነበሩ። ከዚህ አንፃር ካየነው፤ ፍቅር የሚባለው ነገር ከጉዳይ የሚጣፍ ነገር አይደለም።

እዚህ ላይ ያንዲት ሴትና ያንድ ወንድ ፍቅር ለትዳር መሰረት አይደለምን? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ከዘመናዊ ትዳር በተቃራኒ የቀድሞ ትዳር በፍቅር የሚጀምር አልነበረም። ከጋብቻ በፊት ወሲብ ብቻ ሳይሆን ፍቅር ራሱ አይታወቅም። ተያይተው የማያውቁ ልጃገረድና ጎልማሳ በወላጆቻቸው ፈቃድ ይተሳሰራሉ። ሰዎች የሚጋቡት ንብረታቸውን ለማደላደል ከዚያ በተረፈ ወላጆቹን እና አገሩን የሚጦር ልጅ ለማፍራት ነበር። በጭሩ፣ ትዳር ብሔራዊ አገልግሎት ሆኖ ቆይቷል። በዚህ

አገልግሎት ውስጥ የፍቅር ሚና እዚህ ግባ እሚባል አልነበረም።

ይህ ማለት የሴትና የወንድ ፍቅር የሚባል አልነበረም ማለት አይደለም። ሰዎች ያያሉ፣ ይመኛሉ፣ ይሳሳባሉ፣ ፍቅር ይይዛቸዋል፣ ፍቅር ያሳደረባቸውን ስሜትም በተመረጡ ቃላት ይገልጹታል። ብቻ በሆነ ነገር ምክንያት የታሪክ ጸሐፊዎቻችን በየዘመኑ ሲዘንብ የኖረውን የፍቅር ግጥም ለምዝገባ የሚበቃ ሆኖ አላገኙትም። ወይ አደገኛ ነው ብለው ፈርተውታል ወይ አይረባም ብለው ንቀውታል። አደገኛ ነው ብለው ይፈሩት ይሆናል የሚለው ግምቴ ያይልብኛል።

አንድ ማሳያ ላንሳ፤ ያዕቆብ ብሩስ የተባለ የስኮት አሳሽ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላስገለበጠው "የሰሎሞን መዝሙር" ሲጽፍ እንዲህ ይላል፦

> "The song of Solomon is a favorite piece of reading among the old priests, but forbidden to the young ones, to deacons, laymen and women. The Abyssinians believe that the song was made by Solomon in Praise of Pharaoh's daughter and do not think as some of our divines are disposed to so that there is in it any mystery or allegory respecting Christ and the Church."

> "መሐልየ ዘሰሎሞን በአረጋዊ ካህናት ዘንድ የተወደደ ምንባብ ሲሆን ለወጣቶች፣ ለዲያቆናት፣ ለመሃይማን እና ለሴቶች የተከለከለ ነው። አቢሲናውያን ይህ መሐልይ ሰለሞን ለፈርኦን ልጅ ያቀረበው መወድስ ነው ብለው ያምናሉ። አንዳንድ የኛ የሥነመለኮት ሊቃውንት (ከሚያስተምሩት በተቃራኒ) ከክርስቶስ እና ቤተክርስያን ጋር የተያያዘ ምስጢርና ተምሳሌት አለው ብለው አያምኑም።"

ብሩስን የምናምነው ከሆነ፣ በዚያን ዘመን የኖሩት ካህናት መሐልየ ሰሎሞን፣ ሰሎሞን በፈርኦን ሴት ልጅ ውበት ተነሽጦ የጻፈው ግጥም ነው ብለው ያምናሉ። በሥነጽሑፉ ውበት ይደሰቱበታል። ይሁን እንጂ ለዲያቆናት፣ ለወጣቶችና ሴቶች አያካፍሉትም። ንፍገቱ ከየት የመጣ ይሆናል። የእኒህን ዜጎች አእምሮ ያባልጋል ወይም ያስታል ብለው ስለሚሰጉ ሴቶችን ያቀብጣል ወንዶችን ደግሞ ወኔያቸውን ይሰልባል ብለው ፈርተውም ሊሆን ይችላል። ቀስ በቀስ መሐልየ ሰሎሞን የፍቅር



ግጥም ሆኖ መታየቱ ቀረ። ልክ የስኮት ሊቃውንት እንዳደረጉት ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ምስጢርና ተምሳሌት ያዘለ ተደርጎ መተርጎም ጀመረ። ምናልባትም በጊዜው ትልቅ የፍቅር ሥነጽሑፍ ሞዴል ሊሆን ይችል የነበረው ሥራ በቅዱስነት ተጠቀለለ።

የፍቅር ግጥሞች በመደበኛ የታሪክ መዝገብ ውስጥ የማይመዘገቡት ምናልባት በውስጣቸው ያለው ሀሳብ ማህበረሰብ ሊያለማው የሚመኘውን ጀግና ባህርይ (ideal Hero) የሚቃረን ሆኖ ታይቶ ሊሆን ይችላል። ጀግና ማለት የሚያርስ የሚዋጋ ከዚያ የተረፈውን ሕይወቱን ደግሞ ለፈጣሪው መሥዋዕት አድርጎ የሚያቀርብ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር።

የወንድ የክብር ምልክቶች ከውጊያና ካምልኮ ጋር የተቆራኙ ነበሩ። ውበት ልብስና ጌጥ የኒህ ነገሮች መገለጫዎች ናቸው። ለምሳሌ ሹርባ መስራት፣ ጎፈሬ ማሳደግ፣ ከሌቻ ግንባር ላይ ማድረግ የመሳሰሉትን ማንሳት እንችላለን። ዛሬ አስቴር አወቀ "ሱፉን ግጥም አርጎ ተከምክሞ ፀጉሩን" እያለች ስትዘፍን አብሮ ከመዝፈን ውጭ ነውር ነው ብሎ የሚቃወም የለም። ባስቴር አወቀ አያት ዘመን ግን አንድን ሴት በፍቅር ለመሳብ ማጌጥ የሚያዋርድ ተግባር ተደርጎ ይቆጠር ነበር። "ለሴቶች መወደድ ሲል (በሴት ለመወደድ ሲል) የሚያጌጥ ወንድ ለሴት ሲል ይሄን ያህል መጨነቁ ውርደት ነው" ይላሉ ራስ ካሳ ሃይሉ ትውልዳቸውን ለማነፅ በጻፉት የምክር መጽሐፍ።

ደግነቱ ከማህበረሰብ የሥነምግባር ፖሊሶች ጭቆና ያመለጡ ጥቂት የፍቅር ግጥሞች ደርሰውናል። ከኒህ መካከል አንዳንዶቹን ስናጤናቸው የሚገርም ነገር እናገኝባቸዋለን። የሰው ልጅ ተፈጥሮ በአያሌ ዓመታት ሂደት ውስጥ አለመለወጡ ይደንቀናል! ከትልልቅ ዘፈኖች የተቀነጨቡ እኒህን ስንኞች በማሳያነት ላቅርብ፦

> "እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ!
> እምልላችኋለሁ፤
> ውዴን ያገኛችሁት እንደሆነ
> ከፍቅር የተነሳ መታመሜን ንገሩት"

"Jaalachuu ti dhukkuba
maaf arna dhabe"

(ትርጉም)

ፍቅር በሽታ ነው፣
ምነው መላው ጠፋ።

"ፍቅር አጠናገረኝ እንደቀትር ምች
መዳኒት ፈልጉ እምታውቁ ሰዎች"

የመጀመርያው ስንኝ ባለቤት በሰሎሞን ማህሌት ውስጥ የምትገኝ አፍቃሪ ሴት ናት። ሁለተኛዋ ደግሞ ከመቶ ሰማንያ ዓመት በፊት የኖረች ቢሊሌ የተባለች የጉማ ሴት ስትሆን፣ ሶስተኛዋ የዘመናችን አቀንቃኝ እጅግአየሁ ሽባባው ናት። ሶስቱም በተለያየ ዘመን ላይ በተለያየ ቦታ የኖሩ ናቸው። ሶስቱም አይተዋወቁም። ግን ሶስቱም አንድ ያንድ እውነት ተካፋዮች ናቸው። የዮሐንስ አድማሱን ዘይቤ ልዋስና "ዘመን ቢለያቸው፣ ስፍራ ቢያርቃቸው ግጥም አገናኛቸው" ብየ ላሳርግ!

******************

ጉልቤው ባደባባይ፣ ድሃውን ሲበድል
ድምፅህን አጠብድል
ቃል፣ ሩምታ፣ ተኩስ
አውቆ የተዘጋ፣ ጆሮ የሚነድል
ባንዲት ቃል ይጫራል
ያንድ ዘ[illegible]ገድል!



በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋ ብር 70